# ምዕራፍ ፡ ፳፰ ፡ ኤውሮጳ ።

## ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ታሪክ ።

፩ ፤ አሁን ፡ ይኸው ፡ ስለ ፡ እንግሊዝና ፡ ስለ ፡ ዌልስ ፤ ስለ ፡ እስኮትላንድና ፡ ስለ ፡ አየርላንድ ፡ ጥቂት ፡ ነገርኋችሁ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ዋናውን ፡ ነገር ፡ በዚች ፡ ትንሽ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፎ ፡ ለማስረዳት ፡ እጅግ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ደግሞ ፤ ስለ ፡ ነገሥታቱ ፤ ስለ ፡ ነበረው ፡ ጦርነትና ፡ መጋደል ፡ የተቻለኝን ፡ ያህል ፡ ነግሬያችኋለሁ ።

፪ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሳልገልጻቸው ፡ የቀሩ ፡ እጅግ ፡ የሚያስደንቁ ፡ አያሌ ፡ ታሪኮች ፡ አሉ ። ጊዜ ፡ ኑሮኝ ፡ ቢሆን ፡ እጅግ ፡ የሚያሥቃችሁን ፡ ኬልቶች ፡ ከድሩኢድስች ፡ የተማሩትን ፡ ሃይማኖትና ፡ ልማድ ፡ ብነግራችሁ ፡ በወደድሁ ።

፫ ፤ ስለ ፡ ኦዲን ፤ ወይም ፡ ዎዲን ፡ እርሱም ፡ ልዩ ፡ የሆነን ፡ የአሕዛብን ፡ ሃይማኖት ፡ ያቆመና ፡ የሰሜን ፡ ኤውሮጳን ፡ ነገዶች ፡ ያለመንገዱ ፡ የመራቸው ፡ የእስካንዲናቢያን ፡ ጀግና ፡ ነው ። የብረቱን ፡ ባላገሮች ፡ ለጥቂት ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ሃይማኖት ፡ አድርገው ፡ አሳቡን ፡ እንደ ፡ ተቀበሉት ፡ ጊዜ ፡ ቢኖረኝ ፡ ልነግራችሁ ፡ በቻልሁ ። ፰ ፡ ዓመት ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ክርስትና ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ሕዝቡም ፡ መጀመሪያ ፡ የዕንጨት ፡ ግድግዳ ፡ አቁመው ፡ የማያምር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ሠሩና ፡ በኋላም ፡ የንቶችን ፡ ሥራ ፡ አስመስለው ፡ ዛሬ ፡ ሕዝቡ ፡ ለአምልኮታቸው ፡ የሚያገለግሉባቸውን ፡ ሕንፃዎች ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ በነገርኋችሁ ።

፬ ፤ በኤውሮጳ ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ስለሚገኙ ፡ ጊብሲስ ፡ ስለሚባሉ ፤ ልዩ ፡ ዘር ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ሕዝብ ፡ ጊዜ ፡ ባገኝ ፡ ልነግራችሁ ፡ በቻልሁ ። እነዚህ ፡ በተለይ ፡ የሚገኙበት ፡ ስፍራ ፡ በእንግሊዝ ፤ በእስጴን ፤ በሁንጋሪያና ፡ በቦሂሚያ ፡ ነው ። ከንዱ ፡ አገር ፡ ተነሥተው ፡ ወደሌላው ፡ ይዞራሉ ፡ እንጂ ፡ የተወሰነ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ የላቸውም ። ከሩቅ ፡ አገር ፡ መምጣታቸውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከግብጽ ፤ ወይም ፡ ከእስያ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ የሚናገር ፡ አይገኝም ። የሚዞሩባቸው ፡ አገሮች ፡ ሲወድቁና ፡ ሲነሡም ፡ ሲገኙም ፡ እነዚህ ፡ ዘላለም ፡ ዙረታቸውን ፡ እንደ ፡ አዘወተሩ ፡ ይኖራሉ ።

፭ ፤ ሮቢንሁድ ፡ ስለ ፡ ተባለው ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ወንበዴ ፡ ቀማኛ ፡ በጫካ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ስላ ፡ አደረገው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ጊዜ ፡ ኖሮኝ ፡ ቢሆን ፡ ልነግራችሁ ፡ በቻልሁ ። ከዚህ ፡ ቀማኛ ፡ ይልቅ ፡ ልናስባቸው ፡ የሚገባቸው ፡ ስለ ፡ ታወቁ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ልነግራችሁ ፡ በቻልሁ ።

፮ ፤ ደግሞ ፡ የልጆች ፡ የአምልኮት ፡ መዝሙር ፡ የምትባል ፡ ትንሽ ፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ ጻፈ ፡ ስለ ፡ ዶክቶር ፡ ዋት ፡ ልነግራችሁ ፡ በቻልሁ ። እርሱም ፡ ብዙ ፡ ጦርነትን ፡

አሸንፈው ፡ ድል ፡ ካደረጉ ፡ ጀግኖች ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ፡ ሥራ ፡ የሠራና ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ያሳየ ፡ ነው ።

፯ ፤ የሳልቡሪ ፡ ሜዳ ፡ እረኛ ፡ የምትባል ፡ እጅግ ፡ ያማረች ፡ ታሪክ ፡ ያላትን ፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ ጻፈ ፡ ስለ ፡ ሐና፡ የክርስቲያን ፡ መንገድ ፡ የሚባለውን፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ ጻፈ ፤ ስለ ፡ ጆን ፡ ቡኒያን ፡ እጅግ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ታሪክ ፡ ያወጣና ፡ ስለሮቢንስን ፡ ክሩሶ ፡ ድፍሪት ፡ ድርሰት ፡ ያወጣ ፤ ስለ ፡ ዳንኤል ፡ ደ ፡ ፎ ፡ ልንገራችሁ ፡ በቻልሁ ።

፰ ፤ የነዚህን ፡ ሰዎች ፡ ታሪክ ፡ ማንበብ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነው ። ወዳጆቻችን፡ ናቸው ። መኖሪያቸውን ፡ ማወቅ ፡ ምን፡ እንደሚመስሉና፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ አደጋ፡ እንዳገኛቸው ፡ ማወቅ ፡ አለብን ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህና ፡ ሌሎችም ፡ የዚች ፡ የምታስደንቅ ፡ የመልካሚቱ ፡ አገር፡ ታሪክም፡ ቢሆን፡ ለጊዜው፡ ላሁኑ፡ ትቸዋለሁ ።

፱ ፤ አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ አስቤ ፡ እጨምራለሁ ። የእንግሊዝን ፡ ሕዝብ ፡ ታሪክ፡ በመጽሐፍ ፡ ስታነቡ ፡ የሕዝቡን ፡ ጠባይና ፡ አካሄድ ፡ በአገራቸው ፡ ልትማሩት፡ ትችላላችሁ ። የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ እጅግ ፡ ሥራ ፡ ወዳጆች ፡ ናቸው ፤ በቤታቸው ፡ አስተናጋጆችና ፡ ፍቅር ፡ የመላባቸው፡ ናቸው ። ደግሞም ፡ ከሩቅ፡ ለመጡ፡ ችግረኞች ፡ ችግራቸውን ፡ ያቀሉላቸዋል ፡ እንጂ ፡ የቸርነት ፡ ሥራ፡ የሚሠሩት፡ በገዛ ፡ አገራቸው ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙት ፡ ድኆች ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

፲ ፤ እስኮትላንዶች ፡ የገንዘብ ፡ ስስት ፡ ያላቸው ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ። ወደ ፡ አገራቸው ፡ የሄዳችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የምትፈልጉትን ፡ ደሞዝ ፡ እየከፈሉዋችሁ ፡ ልትቀመጡ ፡ ትችላላችሁ ። የእስኮትላንድ ፡ ሰው ፡ ከአገሩ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ሌላ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይከብርና ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይመለሳል ። በገሩም ፡ ደስ፡ ብሎት፡ ይኖራል ። አይሪሾችም፡ ደስ፡ ቢላቸውም ፤ ቢቸገሩም፡ እንደነርሱ፡ ናቸው ።

፲፩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በአገሩ ፡ ወንጌል ፡ ስለ ፡ ተሰበከና፡ ሥልጣኔ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ የሕዝቡ፡ ጠባይ ፡ ወደ ፡ በጎነት ፡ በጣም ፡ ተለውጦዋል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ዎዲን ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡ ?
እርሱ ፡ ያመጣው ፡ የአሕዛብ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
ክርስትና ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የገባው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፪ ፤ ጊብሲስ ፡ የተባሉ ፡ ምንድናቸው ፡ ?
መኖሪያቸው ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?

፫ ፤ ሮቢንሁድ ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡ ?

፮ ፤ ዶክቶር ፡ ዋትስ ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡ ?

፯ ፤ ሌሎች ፡ የከበሩ ፡ ጸሓፊዎች ፡ ምን ፡ ጻፉ ፡ ?

፱ ፤ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፲ ፤ እስኮትላንዶች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፲፩ ፤ አይሪሾችሳ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪፫፬ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ጨለማ ፡ ዘመንና ፡ አዲስ ፡ ስለ ፡ ተገኘው ፡ ዋና ፡ ነገር ።

፩ ፤ ስለ ፡ ኤውሮጳ ፡ በጭሩ ፡ የተረከሁት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነው ። አሳባችሁን ፡ ለማ ነሣሣት ፡ ያህል ፡ ነገርኋችሁ ፤ እኔ ፡ ስለ ፡ አመለከትኋችሁ ፡ ነገዶችና ፡ ስለ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ ብዙ ፡ እንድታነቡ ፡ መራኋችሁ ። በጥንቃቄ ፡ የተማራችሁት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝና ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ትረዱታላችሁ ፤ ብዙዎችን ፡ ነገሮች ፡ ስነግራችሁ ፡ ቈይቼ ፡ ሳልነግራችሁ ፡ የቈየሁ ፡ ጥቂቶች ፡ ነገሮች ፡ አሉኝ ።

፪ ፤ ልብ ፡ ታደርጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሌሎች ፡ ከኤውሮጳ ፡ አገሮች ፡ ከፍሎች ፡ በፊት ፡ ሕዝብ ፡ የነበረበት ፡ አገር ፡ ግሪክ ፡ ብቻ ፡ ሁኖ ፡ ሳለ ፡ ሕዝቡም ፡ ሥልጡኖችና ፡ ኀይ ለኞች ፡ ነበሩ ። እንዲሁም ፡ ሮም ፡ እጅግ ፡ ኀይለኛ ፡ መንግሥት ፡ ሆነና ፡ ግዛቱም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በታወቁት ፡ በዓለም ፡ ክፍሎች ፡ ተዘረጋ ።

፫ ፤ ከአራት ፡ ወይም ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ሮም ፡ ከሌ ሎች ፡ ነገዶች ፡ አንድነት ፡ እንደሌለውና ፡ በሰሜን ፡ ኤውሮጳ ፡ ያሉ ፡ ነገዶች ፡ በእስጳንያ ፤ በጣልያን ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ተዘረጉ ፡ ልብ ፡ ሳታደርጉ ፡ አትቀሩም ። በነዚህ ፡ አገሮች ፡ የተሠራው ፡ ብልሀትና ፡ ትምህርት ፡ ረቂቁም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ ሆነና ፡ ስለ ፡ ጠፋ ፡ መላው ፡ ኤውሮጳ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ አውሬነት ፡ አዘነበለ ።

፬ ፤ ሕዝቡ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፈጽመው ፡ ድንቍርና ፡ ስለ ፡ ነበዛቸው ፡ የአውሬ ፡ ጠባይና ፡ ተናዳጅነት ፡ አደረባቸው ። ስለዚህ ፡ ያ ፡ ዘመን ፡ የጨለማ ፡ ዘመን ፡ ተባለ ። የዕውቀት ፡ ብርሃን ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ እንደዚሁ ፡ እንደጨለመ ፡ ፰፻ ፡ ዘመን ፡ ያህል ፡ ቈየ ። ቀድሞ ፡ ታይቶ ፡ ወደ ፡ አልታወቀ ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ የሥጣኔ ፡ ደረጃ ፡ እስኪደርሱ ፡ ድረስ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምረው ፡ ሕዝቡ ፡ በዕውቀት ፡ ላይ ፡ ዕውቀትን ፡ እየጨመሩ ፡ ሄዱ ።

፭ ፤ አሁን ፡ ምክንያት ፡ አድርጌ ፡ የምናገረው ፡ የክርስቶስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ታሪክ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከመድኀኒታችን ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ፴፫ ፡ ዓ . ም. ወንጌልን ፡ ለማስተማር ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አህጉር ፡ ተበተኑ ። ከነዚህም ፡ የወንጌል ፡ መልክተኞች ፡ ዋና ፡ ሠራተኛና ፡ ጕዳዩ ፡ ይከናወንለት ፡ የነበረው ፡ ጳው ሎስ ፡ ነበር ። እውነተኛውን ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ለመስበክ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተመላለሰ ፡ በትንሽ ፡ እስያ ፡ ውስጥና ፡ በግሪክ ፤ በኋላም ፡ ወደ ፡ ሮምና ፡ ወደ ሌሎችም ፡ ብዙ ፡ አገሮች ፡ ሄዶዋል ። ከክርስቶስ ፡ በኋላ ፡ ፷፪ ፡ ዓመት ፡ በሮም ፡ ሞተ ።

፮ ፤ መጀመሪያ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ የሮም ፡ ነገሥታት ፡ አሳደዱዋቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ወንጌል ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በሮም ፡ መንግሥት ፡ በሚበልጠው ፡ ክፍል ፡ እየገነነችና ፡ እያሸነፈች ፡ ተዘረጋች ። ፫ ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ ክርስትና ፡ ወደ ፡ ብሪ

ታኒያ ፡ ገባች ። እንዲሁም ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በኤውሮጳ ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ ወንጌል ፡ ተሰብኮ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በ፫፻-፮ ፡ ዓመት ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ሃይማኖትን ፡ እስኪቀበል ፡ ድረስ ፡ ከኤውሮጳ ፡ ገዦችና ፡ ነገሥታት ፡ ክርስትናን ፡ የተቀበለ ፡ አል ተገኘም ፡ ነበር ።

፯ ፤ ከዚህ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ክርስትና ፡ በፍጥነት ፡ እየተስፋፋ ፡ ሄደ ። የድሩኢድ ስች ፡ የሚያስፈራ ፡ መሥዋዕታቸውና ፡ ከንቱ ፡ አምልኮታቸው ፡ አንድ ፡ አምላ ክን ፡ ወደ ፡ ማምለክ ፡ ተለወጠ ፤ የአዲንም ፡ አምልኮት ፡ ተናቀና ፡ የመስቀልን ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀበለ ።

፰ ፤ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ የሮም ፡ ጳጳሳት ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ዓለምን ፡ እን ዳሸነፈ ፡ በተመለከቱ ፡ ጊዜ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ኀይል ፡ ለማግኘት ፡ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ የቤተ ክርስቲያን ፡ አለቆች ፡ ለማድረግ ፡ አሰቡ ። ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እያሉ ፡ ሁለጊዜ ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ለክፉ ፡ መሣሪያ ፡ ሊያደርጉበት ፡ ብዙ ፡ ኀይል ፡ አገኙ ።

፱ ፤ እንዲሁም ፡ እያደር ፡ ሥልጣናቸው ፡ እየተዋረደ ፡ ተክርስቲያኖችም ፡ የሚ በዙት ፡ ክፍል ፡ ፕሮቴስታንት ፡ የተባሉ ፡ ተነሡባቸው ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ በሮም ፡ ካቶሊካውያን ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ በሌሎች ፡ ላይ ፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ ሥልጣን ፡ የለ ውም ።

፲ ፤ በእስጳንያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ኢንኲሲሽን ፡ ማለት ፡ ምርመራ ፡ ነገር ፡ አመለክቻለሁ ። ይህም ፡ እውነተኛ ፡ የጳጳስ ፡ ወይም ፡ የካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ተከታይ ፡ ያልሆነውን ፡ ሰው ፡ እየያዙ ፡ ለመመርመርና ፡ ለመፈተን ፡ የሚያቀ ርቡበት ፡ የተሰወረ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

፲፩ ፤ ይህም ፡ ደንብ ፡ የቆመው ፡ በሺ ፡ ፪፻፲፭ ፡ ዓ. ም. ፫ኛ ፡ ኢኖሲንት ፡ በተባለው ፡ ጳጳስ ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይገለጣል ። ከዚያ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ይህ ፡ ልማድ ፡ እየተዘረጋ ፡ ሄደ ። ወዲያው ፡ በሺ ፡ ፬፻፹፬ በእስጳንያ ፡ እንዲሁ ፡ ይደረግ ፡ ጀመር ። ከዚህ ፡ ትልቅ ፡ ኀይል ፡ አገኘና ፡ ክፉ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ታይቶ ፡ ያልታወቀ ፡ የግፍ ፡ ፍርድ ፡ ይደረግ ፡ ጀመር ።

፲፪ ፤ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ ክፍ ፡ ያለው ፡ ገዢ ፡ እንዲሆን ፡ አሳቡን ፡ ለመደገፍ ፡ ይኸው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ የተወደደ ፡ መሣሪያ ፡ ሆነው ። የካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ በተዘረጋበት ፡ በኤውሮጳ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ገብቶአል ፤ ታውቆአል ። በየትም ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ በእስጳንያ ፡ እንደ ፡ ተሠራው ፡ ያለ ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ አል ተሠራም ። ይኸውም ፡ ልማድ ፡ እስከ ፡ ሺ፰፻፴፬ ፡ ድረስ ፡ ፈጽሞ ፡ አልጠፋም ።

፲፫ ፤ በኤውሮጳ ፡ ስለ ፡ አሉት ፡ ገዳማትና ፡ መነኰሳት ፡ ነገር ፡ ለማመልከት ፡ የተ መቸ ፡ ጊዜ ፡ አላገኘሁም ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ሊታወቁ ፡ ይገባል ። በብዙ ፡ አገሮች ፡ አያሌ ፡ ሰዎች ፡ ዋና ፡ የዕለት ፡ ሥራቸውን ፡ እየ ተዉ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ተዘግተው ፡ የሚኖሩ ፡ ብዙዎች ፡

ናቸው ። በእስያ ፡ እንደሚደረግ ፡ የብራማ ፡ የፎ ፤ የላማ ፤ የሙሐመድም ፡ ወገ
ኖች ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ እንደዚሁ ፡ የሚያደርጉ ፡ ይገኛሉ ። ጣዖታትን ፡ ከሚያመልኩ ፡
ከጥንት ፡ ግብፃውያን ፤ ከግሪክ ፤ ከሮማውያንም ፡ ወገን ፡ እንዲሁ ፡ ያደርጋሉ ።
በፊተኛው ፡ ዘመንም ፡ ከአይሁድና ፡ ከክርስቲያኖች ፡ ወገን ፡ እንደዚሁ ፡ ተደርጓል ።
፲፬ ፤ ፫፻—፭ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ መጀመሪያ ፡ ገዳም ፡ የሚባል ፡ ነገርን ፡
በላይኛው ፡ ግብፅ ፡ የመሠረተ ፡ ቅዱስ ፡ እንጦንስ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ነው ። በዚህም ፡
ገዳም ፡ መናንያን ፡ ገብተው ፡ በጸሎት ፡ የሚኖሩባቸው ፡ ብዙ ፡ ጉጆዎች ፡ ተሠር
ተው ፡ ነበር ። ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ገዳም ፡ በ፫፻፷ ፡ ዓመት ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ቅዱስ ፡
ማርቲን ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ አቁሞ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ካቶሊካውያን ፡
በሚኖሩበት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ሥርዓት ፡ በዝተውና ፡ ጸንተው ፡ ኖሩ ።
ከ፰ ፡ እስከ ፡ ፲፭ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ታላቅ ፡ ብርታት ፡ አግኝተው ፡
ለሥራቸው ፡ የሚሆኑና ፡ ብዙ ፡ አድርገው ፡ የሚታዩ ፡ ታላላቅ ፡ ቤቶችን ፡ ኋመሥ
ራት ፡ በቁ ።
፲፭ ፤ አንዳንዶችም ፡ ገዳም ፡ አንዳንዶችም ፡ የመነኰሳት ፡ መኖሪያ ፡ ተባሉ ።
በሚበዙት ፡ ቤቶች ፡ መነኰሳትና ፡ ድኆች ፤ ለማኞች ፡ ይኖሩበታል ። በሌሎችም ፡
ቤቶች ፡ የሴት ፡ መነኰሲቶች ፡ ይኖሩበታል ። የነዚህም ፡ ቤቶች ፡ ፍራሽ ፡ በእንግ
ሊዝ ፤ በፈረንሳይ ፤ በጀርመንና ፡ በሌሎችም ፡ በኤውሮጳ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይገኛሉ ። ፊት ፡ በገዳም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ በጸሎት ፡ ተጠምደው ፡
በቀላል ፡ ኑሮ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ በተድላና ፡ በደስታ ፡ የሚኖሩ ፡ በገዳም ፡
ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሁነው ፡ ተገኙ ። ገዳማትም ፡ የአዱኛ ፡ ማከማቻ ፡ ሆኑ ። በኋላም ፡
ከመነኰሳትና ፡ ከሴት ፡ መነኰሲቶች ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ውስጥ ፡
እንዳይገባ ፡ ተከለከለ ። ይህንንም ፡ ማድረጋቸው ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ምንኵስና ፡ ተገባ ፡
በኋላ ፤ የሚኖረው ፡ በተድላና ፡ በደስታ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ከዓለም ፡ ዐይን ፡ ለመ
ሰወር ፡ ብለው ፡ ነው ።
፲፮ ፤ ይህንንም ፡ ሥርዓት ፡ በጣም ፡ እንዲበረታ ፡ አድርገው ፡ የደገፉት ፡ ጳጳሳት ፡
ናቸው ። በ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የተደረገው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መታደስ ፡
እርሱም ፡ የካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ጥፋት ፡ የሆነበት ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ የገዳሞች ፡
ደንብና ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ ለመውደቅ ፡ አዘነበሉ ። በሺ ፡ ፭፻፴፱ ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡
ገዳማት ፡ የተባሉ ፡ ተሻሩ ፤ በሺ ፯፻፺ ፡ ከፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ ተሻገሩ ።
በኤውሮጳ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ የነበሩት ፡ ገዳማት ፡ ሁሉ ፡ ሥራቸው ፡ ታገደ ።
ነገር ፡ ግን ፡ በኢጣልያና ፡ በእስጳንያ ፡ እስካሁን ፡ ሥራቸውን ፡ ይሠራሉ ።
፲፯ ፤ ጥንት ፡ ዘመን ፡ ጦርነት ፡ የሚደረገው ፡ ያለ ፡ ጠመንጃና ፡ ያለ ፡ መድፍ ፡
ነበር ፤ ግሪኮችና ፡ ሮማውያን ፡ ለጦርነት ፡ ሲወጡ ፡ ጐራዴና ፡ መጥረቢያ ፤ ጦር ፤ ለመመ
ከቻም ፡ ጋሻ ፡ ይዘው ፡ ይወጡ ፡ ነበር ። የግብፅና ፡ የካርታጎ ፡ የፋርስም ፡ ወታደሮች ፡
እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ መሣርያ ፡ ነበራቸው ። በሺ ፡ ፫፻፴ ፡ ባሩድ ፡ ተገኘና ፡ በጦርነት ፡

ጊዜ ፡ ውጊያው ፡ በጠመንጃ ፡ ሆነ ። በሺ ፡ ፫፻፵፮ ፡ ክሬሲ ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ በደረጉ ፡ ጊዜ ፡ መጀመሪያ ፡ ጠመንጃን ፡ የሠሩ ፡ እንግሊዞች ፡ ናቸው ። እንዲሁም ፡ ንጉሡ ፡ ኤድዋርድ ፡ ድል ፡ እንዲያደርግ ፡ በጣም ፡ የረዱት ፡ አራት ፡ መድፎች ፡ ነበሩት ።

፲፰ ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ጠመንጃ ፡ በፍጥነት ፡ እየተሠራ ፡ በረከተ ። የመዋጋት ፡ ብልሀትም ፡ ሁሉ ፡ ተለወጠና ፡ ቀስትና ፡ ፍላፃ ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ ወዲያው ፡ ተጣለ ። የሚዋጉት ፡ ወታደሮች ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተቃርበው ፡ መዋጋታቸው ፡ ቀርቶ ፡ በሩቅ ፡ ሆነው ፡ በጠመንጃ ፡ ተኩሰው ፡ መጣልን ፡ ተማሩት ።

፲፱ ፡ በሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የተገኘው ፡ ታላቁ ፡ ብልሀት ፡ ሁለጊዜ ፡ የሰሜንን ፡ የመሬት ፡ ራስ ፡ የሚያመለክት ፡ የመርከበኞች ፡ ኮምፓስ ፡ ነው ። መርከበኞች ፡ በ ጥልቁ ፡ ባሕር ፡ ለመተላለፍ ፡ መንገዳቸውን ፡ የሚያመለክታቸው ፡ ይህ ፡ የሚጠቅም ፡ መሣርያ ፡ ተገኝቶ ፡ በሺ ፡ ፬፻፲ ፡ ዓ. ም. ይሠሩበት ፡ ነበር ።

፳ ፡ እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ በሺ ፡ ፬፻፵፬ ፡ የጽሕፈት ፡ መኪና ፡ ብልሀት ፡ ተገኘ ። ከዚያ ፡ በፊት ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ የሚጻፉት ፡ በብርዕ ፡ ነበር ። በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ያንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ግልባጭ ፡ ዋጋ ፡ ዛሬ ፡ ላንድ ፡ መሬት ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ ቤት ፡ የሚከፈለውን ፡ ዋጋ ፡ ያህል ፡ ያወጣ ፡ ነበር ። መጽሐፍ ፡ ለማግኘት ፡ እጅግ ፡ ችግር ፡ ነበርና ፡ ለማንበብ ፡ ያህል ፡ የሚማሩት ፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ ጥቂቶች ፡ ነበሩ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ ከኤውሮጳ ፡ ሕዝብ ፡ አስቀድመው ፡ ገብተው ፡ ስፍራ ፡ የያዙ ፡ የትኞች ፡ ናቸው ፡ ? ሮም ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?

፪ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ አራት ፡ ወይም ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፫ ፡ የጨለማ ፡ ዘመን ፡ የሚባለው ፡ የትኛው ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ?
ለመንቀሳቀስ ፡ ትምህርት ፡ የተጀመረው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፬ ፡ ክርስቶስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ? ሐዋርያቱ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፭ ፡ መጀመርያ ፡ ሮማውያን ፡ ክርስቲያኖችን ፡ እንደምን ፡ አድርገው ፡ ተቀበሉዋቸው ፡ ?
በቢሪታንያ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ የታወቀው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
በ፫፻—፮ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፮ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ማደግ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፯ ፡ ጳጳስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፰ ፡ ጵሮቴስታንቶች ፡ የሚባሉት ፡ እነማን ፡ ነበሩ ፡ ? ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ጳጳስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፲ ፡ የሃይማኖት ፡ ምርመራ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፲፩ ፤ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ የሰጠ ፡ የተኛው ፡ ጳጳስ ፡ ነው ፡ ? የተደረገው፡ምን፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
በእስጳንያ ፡ የቆመው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? በዚያ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፲፪ ፤ የሃይማኖት ፡ ምርመራ ፡ በወዴት ፡ አገር ፡ ገባ ፡ ?

፲፫ ፤ እጅግ ፡ ክፉት ፡ የተሠራው ፡ በየት ፡ አገር ፡ ነው ፡ ?
በብዙ ፡ አገሮች ፡ እንደምን ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ፡ ?

፲፬ ፤ የመጀመርያውን ፡ ገዳም፡ያቆመ፡ማነው፡? የቆመውስ፡ምን፡ጊዜ፡ነው፡? ምን ፡ አለበት ፡ ? በፈረሳንይ ፡ አገር፡የመነኰሳትን ፡ ገዳም ፡ የመሠረተ ፡ ማነው ፡ ? እስካሁን ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ገዳም ፡ ነው ፡ ?

፲፭ ፤ ማን ፡ አኖራቸው ፡ ? የወንድ ፡ መነኰሴና ፡ የሴት ፡ መነኰሲቶች ፡ እንዴት ፡ ይኖራሉ ፡ ? በኋላ ፡ እንደምን ፡ ይኖራሉ ፡ ?

፲፮ ፤ እነዚህን ፡ የመነኰሳት ፡ ሕግጋት ፡ የሠራቸው ፡ ወይም ፡ ያቋቋማቸው ፡ ማነው ፡ ? የገዳሞች ፡ ሥርዓት፡እየተዳከመ፡የሄደው ፡ ምን፡ጊዜ፡ነው፡? ተእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ፈጽሞ ፡ የተሻረው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ከፈረንሳይስ ፡ ? እስካሁን ፡ በወዴት ፡ ይኖራሉ ፡ ?

፲፯ ፤ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ጦርነት ፡ ነበር፡? የጦር ፡ መሣርያስ፡? ባሩድ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተገኘ ፡ ? መጀመርያ ፡ መድፍ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ይሠራ ፡ የነበረ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፲፰ ፤ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፲፱ ፤ ባሁን ፡ ዘመን ፡ የተገኘ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ምንድነው፡?
የመርከበኞች፡ኮምፓስ ፡ መጀመርያ፡የተሠራበት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፳ ፤ የጽሕፈት ፡ መኪና ፡ ብልሀት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተገኘ ፡ ?
ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ መጻሕፍት ፡ እንደምን ፡ ይደረጉ ፡ ነበር ፡ ?

# ምዕራፍ ፣ ፳ ፣ አሜሪካ ።

## ስለ ፤ አሜሪካ ።

፩ ፤ እስከ ፣ አሁን ፣ እስያ ፤ አፍሪካ ። ኤውሮጳ ፣ በተባሉት ፣ በ፫ቱ ፣ ታላላቅ ፣ የም ሥራቅ ፣ የብሶች ፣ ላይ ፣ ሠርተናል ፤ አሁን ፣ እነዚህን ፣ አገሮች ፣ እንተውና ፣ የእ ንትላቲክን ፣ ውቅያኖስ ፣ ተሻግረን ፣ የአሜሪካንን ፣ የብስ ፣ እንጐብኘው ።

፪ ፤ በካርታው ፣ ላይ ፣ እንደምታዩት ፣ አገሩ ፣ ከ፪ት ፣ ላይ ፣ የተከፈለ ፣ ነው ። ይኸ ውም ፣ የሰሜንና ፣ የደቡብ ፣ አሜሪካ ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ። እነዚህም ፣ ሁለት ፣ የብሶች ፣ ደሪን ፣ በተባለ ፣ በቀጭን ፣ ስርጥ ፣ ይገናኛሉ ። ይህም ፣ ቀጭን ፣ ስርጥ ፣ (መገናኛ ፣ )ስድሳ ፣ ማይል ፣ የሚሆን ፣ ስፋት ፣ አለው ። ይህ ፣ እጅግ ፣ ሰፊ ፣ የሆነ ፣ አገር ፣ በስፋት ፣ ዘጠኝ ፣ ሺሕ ፣ ማይል ፣ ይሆናል ። ይህም ፣ ማለት ፣ እስያን ፣ ሊያ ህል ፣ ጥቂት ፣ ይቀረዋል ። የሕዝቡም ፣ ቍጥር ፣ ፺፪ ፣ ሚሊዮን ፣ ለመሆን ፣ ይቃ ረባል ።

፫ ፤ በሰሜን ፣ አሜሪካ ፣ በኩል ፣ ከልክ ፣ ያለፈ ፣ ቅዝቃዜ ፣ አለው ። በባሕር ፣ ተወ ስኖአልና ፣ ሰዎች ፣ እንደሚያስቡት ፣ ወደ ፣ ሰሜን ፣ ምድር ፣ ራስ ፣ አይደርስም ። በዚያው ፣ በኩል ፣ ሕዝብ ፣ ያለበት ፣ ግሪንላንድ ፣ የተባለው ፣ ብርዳም ፣ አገር ፣ ቀድሞ ፣ ከሰሜን ፣ የብስ ፣ ጋር ፣ የተያያዘ ፣ ነው ፣ ተብሎ ፣ ይታሰብ ፣ ነበር ። አሁን ፣ ግን ፣ ለብቻው ፣ የተለየ ፣ ቢሆን ፣ እንጂ ፣ ከሌላ ፣ የብስ ፣ ጋር ፣ የተያያዘ ፣ አለመ ሆኑ ፣ ታወቀ ።

፬ ፤ በደቡብ ፣ አሜሪካ ፣ ያሉ ፣ አገሮች ፣ ከዚህ ፣ ይከተላሉ ። የአይስላንድ ፣ ደሴት ፤ ግሪንላንድ ፤ ኤስኪሞችና ፣ ሌሎችም ፣ የህንድ ፣ ወገኖች ፣ የሚኖሩባቸው ፣ የፖ ላር ፣ አውራጃዎች ፣ ብሪቲሽ ፣ አሜሪካ ፤ ረሺያን ፣ አሜሪካ ፣ ዩናይትድ ፣ እስቴ ትስ ፤ ሜክሲኮ ፣ ጉታማላ ፣ ናቸው ።

፭ ፤ በደቡብና ፣ በሰሜን ፣ አሜሪካ ፣ መኻከል ፣ ዌስት ፣ ኢንዲስ ፣ የተባሉ ፣ ያማሩ ፣ ደሴቶች ፣ አሉ ። በደቡብ ፣ አሜሪካ ፣ ውስጥ ፣ ያሉት ፣ አገሮች ፣ ቬኒዙኤላ ፣ ኙግ ሬናዳ ፤ ኤኩዋቶር ፣ ፔሩ ፤ ቦሊቢያ ፤ ቺሌ ፤ የዩናይትድ ፣ እስቴትስ ፣ አውራጃ ዎች ፣ ናቸው ። እነዚህም ፣ ሁሉ ፣ ሬፑብሊክ ፣ ናቸው ። ብራዚል ፣ ቀድሞ ፣ የፖ ርቱጋል ፣ ግዛት ፣ ነበር ። ዛሬ ፣ ግን ፣ ነጻ ፣ ወጥቶ ፣ በገዛ ፣ ራሱ ፣ አዳሪ ፣ ሆኖ ፣ የን ጉሠ ፣ ነገሥት ፣ አገር ፣ ተብሎዋል ። በደቡብ ፣ አሜሪካ ፣ ፓታጎኒያ ፣ በተባለው ፣ አገር ፣ ጥቂት ፣ ያልሠለጠኑ ፣ ሕዝቦች ፣ አሉበት ።

፮ ፤ በሰሜን ፣ አሜሪካ ፣ ወገን ፣ በጣም ፣ ብርድ ፣ ነው ፣ ብያለሁ ፤ በዚሁ ፣ አገር ፣ ምንም ፣ ዛፍ ፣ አይታይበትም ። ከመቱ ፣ ውስጥ ፣ ፱ ፣ ወር ፣ ባሕሩ ፣ ይረጋና ፣ እንደ በረዶ ፣ ይሆናል ። ሕይወት ፣ ያለው ፣ ፍጡር ፣ በዚያ ፣ ሊኖር ፣ አይችልም ። በበጋ ፣

ጊዜም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነጭ ፡ አንበሳ ፡ ወይም ፡ ብቻውን ፡ የሚኖር ፡ ሬንዲር ፡ የሚሉት ፡ ያጋዘን ፡ ዐይነት ፡ እንስሳ ፡ የደንጊያ ፡ ልብስ ፡ ሲግጥ ፡ ይታያል ።

፯ ፤ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወገን ፡ ብትመለከቱ ፡ ዛፍና ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ መልተዋል ። በውሃ ፡ ላይ ፡ የሚዋኙ ፡ ወፎችም ፡ ይታያሉ ።

፰ ፤ በዚሁ ፡ አውራጃ ፡ ኤስኪሞ ፡ የሚባሉትንና ፡ ቺፑዋ ፡ ኢንዲያንስ ፡ የተባሉትን ፡ ሕዝብ ፡ ታያላችሁ ። ወደ ፡ ከናዳ ፡ ስትደርሱ ፡ ፍሬ ፡ የምትሰጠውን ፡ አገር ፡ ታያላችሁ ። ወደ ፡ ዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ብትደርሱ ፡ አየሩ ፡ ጥሩ ፡ ነው ። በሚክሲኮ ፡ ባሕር ፡ ዙሪያ ፡ ዌስት ፡ ኢንዲስ ፡ በሚባለው ፡ አገርና ፡ በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ሁልጊዜ ፡ አየሩ ፡ እንደበጋ ፡ ጊዜ ፡ ይመስላል ።

፱ ፤ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ራቅ ፡ ያላችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብርዳም ፡ ነው ። ኬፕሆርን ፡ ወደ ተባለው ፡ አውራጃ ፡ የደረሳችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሃው ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ የሚረጋበት ፡ አገር ፡ ነው ። ክረምቱም ፡ ከመቱ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፡ ነው ። በአሜሪካ ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ እጅግም ፡ አይበዙ ። ጎሽ ፣ ድኵላ ፣ የዱር ፡ አራዊት ፣ የዱር ፡ በግ ፣ አጋዘን ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ሰስና ፡ ሚዳቋ ፣ አያሌ ፡ ዐይነት ፡ ዳልግ ፡ አንበሳ ፣ ቀበሮ ፣ ተኵላ ፣ ሌሎችም ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ አዕዋፍ ፡ ሁሉ ፡ ባሜሪካ ፡ ይገኛሉ ።

፲ ፤ ብዙዎች ፡ የአሜሪካ ፡ የቤት ፡ እንስሶች ፡ መጀመሪያ ፡ አገሩ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ አልተገኙም ። ኙፋውንድላንድ ፡ የተባለው ፡ ውሻ ፣ ሌሎችም ፡ ፩ ፡ ወይም ፡ ፪ ፡ ዐይነት ፡ የሆኑ ፡ በዚያው ፡ አገር ፡ የተገኙ ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የቤት ፡ እንስሶችን ፣ በጐችንና ፡ ፍየሎችን ፣ አህዮችን ፣ በቅሎችንና ፡ ፈረሶችን ፣ ዶሮችንና ፡ ድመቶችን ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ ያረቡዋቸው ፡ ከኤውሮጳ ፡ አምጥተው ፡ ነው ። ከቤት ፡ እንስሶች ፡ ተርኪ ፣ ዝይና ፡ ዳክዬ ፡ ግን ፡ ከዚያው ፡ የተገኙ ፡ ናቸው ።

፲፩ ፡ የአሜሪካ ፡ ሕዝብ ፡ ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ ክፍል ፡ ናቸው ። የመጀመርያዎቹ ፡ ቀድሞ ፡ አሜሪካ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ እዚያው ፡ አገሩ ፡ ውስጥ ፡ ተበትነው ፡ የተገኙት ፡ እንዲያንስ ፡ ይባላሉ ። እነዚህም ፡ በየነገዳቸው ፡ ተከፍለው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ እየሆኑ ፡ በቋንቋም ፡ የተለያዩ ፡ ነበሩ ። ሁለተኞዎቹ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘመን ፡ ከኤውሮጳ ፡ እየሄዱ ፡ በዚያው ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ የኤውሮጳውያን ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ። በነዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ከአፍሪካ ፡ በባርነት ፡ የመጡት ፡ አያሎች ፡ ሚሊዮን ፡ የሚሆኑ ፡ ሻንቅሎች ፡ አሉበት ።

፲፪ ፤ አሜሪካ ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ነገር ፡ የታወቀ ፡ ነው ። አንደኛ ፡ ሰፋፊ ፡ ሐይቆች ፣ ሁለተኛ ፡ ረጃጅም ፡ ወንዞች ፣ ሦስተኛ ፡ በዓለም ፡ የታወቁ ፡ የተያያዙ ፡ ተራሮች ፡ ናቸው ። ሰፊ ፡ ሐይቅ ፡ የተባለው ፡ ሌክሱፔሪዮር ፡ ነው ። ረጅም ፡ ወንዝ ፡ የተባለው ፡ ሚሲሲፒ ፡ ነው ። የተያያዘ ፡ ተራራ ፡ የተባለው ፡ በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ ያለው ፡ አንድስ ፡ የተባለው ፡ በጉታማለ ፡ ያለው ፡ ጕርዲሊራና ፡ ሚክሲኮ ፣ በዩናይት ፡ እስቴትስ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሮኪ ፡ ማውንቴን ፡ የተባለው ፡ ነው ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ የአሜሪካ ፡ የብስ ፡ ምን ፡ አለበት ፡ ? የአምሪካ ፡ ስፋትና ፡ የሕዝብ ፡ ብዛት ፡
እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፪ ፤ በሰሜን ፡ አሜሪካ ፡ ክፍል ፡ የታወቀው ፡ ምንድነው ፡ ?
ግሪንላንድ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?
፫ ፤ የሰሜን ፡ አሜሪካ ፡ አገሮች ፡ እንዴት ፡ ናቸው ፡ ?
፬ ፤ የምዕራብ ፡ ኢንዲስ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?
የደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ ክፍል ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ብራዚልስ ፡ ?
፭ ፤ የሰሜን ፡ አሜሪካ ፡ ክፍል ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፮ ፤ በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ የአታክልት ፡ ሕይወት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፯ ፤ ነገደ ፡ ኢንዲያን ፡ የተባሉት ፡ እንዴት ፡ ናቸው ፡ ?
የደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ አውራጃ ፡ አየሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ።
፰ ፤ ኬፕሆርን ፡ የሚባለው ፡ አውራጃ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?
የአሜሪካ ፡ እንስሶችና ፡ ወፎች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?
፲ ፤ እንዴት ፡ ያሉ ፡ እንስሶች ፡ ይገኛሉ ፡ ?
የቀንድ ፡ ከብት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ያገሩ ፡ ወፎች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?
፲፩ ፤ በአሜሪካ ፡ ስለሚገኙት ፡ ስለሁለት ፡ ዐይነት ፡ ሕዝብ ፡ ተናገር ።
፲፪ ፤ አሜሪካ ፡ ስመ ፡ ጥሩነቱ ፡ በምንድነው ፡ ?
የሚበልጠው ፡ ሐይቅ ፡ ማነው ፡ ?
የሚሲሲፒ ፡ ወንዝና ፡ አንድስ ፡ የሚባለው ፡ ተራራ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፱፩ ፡ አሜሪካ ።

### ልለ ፡ ጥንታውያን ፡ የአሜሪካ ፡ ባላገሮች ።

፩ ፤ እንደነዚህ ፡ ያሉ ፡ ያማሩትን ፡ ከተሞች ፡ እንደ ፡ በስቶን ፤ ኒዮርክ ፤ ፊላዲልፊያ ፤ ባልቲሞር ፤ ቾአርሊንስ ፤ ሉዊስቬል ፤ ሲንሲናቲም ፡ ያሉትን ፡ ደግሞም ፡ መንደሮችና ፡ ከተሞች ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ፍንጥቅጥቅ ፡ ያሉባቸውን ፡ ሰፋፊ ፡ አገሮች ፡ ከኤውሮጳና ፡ ከእስያ ፤ ከአፍሪካም ፡ መጥቶ ፡ የተመለከታቸው ፡ ሰው ፡ በውነት ፡ አሜሪካ ፡ የታወቀው ፡ የዛሬ ፡ ፬፻ ፡ ዓመት ፡ አይደለም ፡ ይላል ።

፪ ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በገሩ ፡ ኢንዲያን ፡ የተባሉ ፡ ብዙ ፡ ነገዶች ፡ ነበሩበት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መጻሕፍት ፡ የሌላቸው ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ የሌላውን ፡ የዓለም ፡ ሁኔታ ፡ አያውቁም ፡ ነበር ። ከወዴት ፡ እንደመጡ ፤ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ምን ፤ ጊዜ ፡ እንደገቡ ፡ እርግጠኛውን ፡ ለመናገር ፡ አይችሉም ።

፫ ፤ በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ ወገን ፡ ኤስኪሞ ፡ የሚባሉ ፡ ሕዝብ ፡ ዘሮች ፡ ይኖሩበት ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ይገልጻል ። እነዚህም ፡ ከሌሎቹ ፡ ኢንዲያን ፡ ከሚባሉት ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ። ላጵላንደርስ ፡ ከሚባሉት ፡ ወገኖች ፡ ጋር ፡ ቅርብ ፡ ይመስላሉ ። ስለዚህ ፡ በፖል ፡ አውራጃ ፡ የሰፈሩ ፡ ሕዝብ ፡ ጥንት ፡ ከኤውሮጳ ፡ በጀልባ ፡ እየመጡ ፡ ወደዚሁ ፡ የገቡ ፡ ይመስላል ።

፬ ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ እንዲደረግ ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡ ይገለጣል ። በስምንተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኖርዌጂያን ፡ አይስላንድን ፡ ማግኘታቸውና ፡ በዘጠነኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በግሪንላንድ ፡ መቀመጣቸው ፡ ከታወቀ ፡ እንግዲያስ ፡ ያ ፡ የአሜሪካ ፡ ክፍል ፡ የተገኘው ፡ ትንሽ ፡ የባሕር ፡ መንገድ ፡ ዕውቀት ፡ ባላቸው ፡ በሰሜን ፡ ኤውሮጳች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይታወቃል ።

፭ ፤ ኢንዲያንስ ፡ የተባሉት ፡ ሕዝብ ፡ ወደዚህ ፡ አገር ፡ (አሜሪካ )እንዴት ፡ ደረሱ ፡ ቢባል ፡ የፓስፊክ ፡ ውቅያኖስን ፡ ካርታ ፡ ብትመለከቱ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ አሜሪካና ፡ እስያ ፡ በጣም ፡ የተቃረቡ ፡ መሆናቸውን ፡ ታያላችሁ ። የቤሪንግ ፡ መሸጋገሪያ ፡ ብቻ ፡ ይለያቸዋል ። ይኸውም ፡ ስፋቱ ፡ ሰማንያ ፡ ማይል ፡ ይሆናል ።

፮ ፤ አሁንም ፡ በጠባቡ ፡ መልካ ፡ ማዶ ፡ ለማዶ ፡ ሁነው ፡ የተቃረቡ ፡ ሕዝብ ፡ በትንሽ ፡ መርከቦቻቸው ፡ እየሆኑ ፡ ከጐረቤቶቻቸው ፡ ይገናኛሉ ። ከታርታሮች ፡ ወገን ፡ የሆኑ ፡ ነገዶ ፡ እስያ ፡ ቤሪኝ ፡ በተባለው ፡ መልካ ፡ እየተሻገሩ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ይገቡ ፡ ነበር ፡ ቢባል ፡ ሊታመን ፡ ይቻላል ። እነዚህም ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድ ፡ ተጠራቅመው ፡ የሚሻገሩ ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩ ። የአሜሪካ ፡ ምድር ፡ በሕዝብ ፡ ሲመሠረት ፡ እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ነው ።

፯ ፤ የደቡብ ፡ እስያ ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ የደረሱት ፡ በታላቁ ፡ በፓስፊክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ከደሴት ፡ ወደ ፡ ደሴት ፡ እየተሸጋገሩ ፡ እንደሚያደርጉ ፡ እንዲሁም ፡ ወደመኻከል ፡ አሜሪካ ፡ ደርሰዋል ። በውቅያኖስ ፡ ደሴቶች ፡ ላይ ፡ የሚኖሩት ፡ ሕዝብ ፡ መሸጋገሪያ ፡ ጀልባ ፡ ወይም ፡ ታንኳ ፡ መሥራት ፡ ይችላሉ ።

፰ ፤ የአሜሪካን ፡ ኢንዲያንና ፡ የእስያ ፡ ነገድ ፡ ይመሳሰላሉ ፡ ለማለት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አለ ። ልማዳቸው ፡ ሁሉ ፡ በእስያ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ነው ። ለኤውሮጳና ፡ ለአፍሪካ ፡ የመጀመርያዎቹን ፡ ሕዝብ ፡ የሰጠች ፡ እስያ ፡ እንዲሁ ፡ ለአሜሪካም ፡ መጀመርያ ፡ ጠረፍዋን ፡ የረገጡላትን ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ሰጠች ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ የዛሬ ፡ ፫፻፶ ፡ ዓመት ፡ አሜሪካ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ነበር ፡ ?

፪ ፤ እንዲያንስ ፡ ሕንዶች ፡ የተባሉት ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?

፫ ፤ ኤስኪሞ ፡ የሚባሉት ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?
የማን ፡ ወገን ፡ ይመስላሉ ፡ ?

፬ ፡ ኖርዌጂያን ፣ የተባሉት ፣ እንዴት ፣ ያሉ ፣ ናቸው ፣ ?
፭ ፡ እስያንና ፣ አሜሪካንን ፣ ምን ፣ ይሉዋቸዋል ፣ ? ስፋታቸው ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
፮ ፡ ለማመን ፣ ምን ፣ ምክንያት ፣ አለ ፣ ?
፯ ፡ የመኻከል ፣ አሜሪካ ፣ ክፍል ፣ ሰው ፣ ያለበት ፣ መምሰሉ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
፰ ፡ ሕንዶቻችን ፣ ማነን ፣ ይመስላሉ ፣ ፤ የአሜሪካ ፣ ሕዝብ ፣ መሠረት ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፻፳፱ ፣ አሜሪካ ።

### ስለ ፣ አሜሪካ ፣ መገኘት ።

፩ ፡ የጥንት ፣ የካርታጎ ፣ ሰዎች ፣ የደቡብ ፣ አሜሪካን ፣ አግኝተው ፣ በዚያ ፣ ይኖሩ ፣ ነበር ፣ እየተባለ ፣ ማስረጃ ፣ የሌለው ፣ ነገር ፣ ይነገር ፣ ነበር ። ደግሞ ፣ ሞንት ፣ ቬዲዎ ፣ በተባለ ፣ ስፍራ ፣ ተቆፍሮ ፣ ስለ ፣ ፑኒክ ፣ የተጻፈ ፣ ነገር ፣ ተገኘ ፣ ይባላል ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ይህም ፣ ቢሆን ፣ ተገኝቷል ፣ የተባለው ፣ ሁሉ ፣ ከተረሳ ፣ ሁለት ፥ ወይም ፣ ሦስት ፣ ሺ ፣ ሕ ፣ ዓመት ፣ ስለ ፣ አለፈበት ፣ እውነትነቱ ፣ ያጠራጥራል ። ነገር ፣ ግን ፣ መጀመሪያ ፣ የሰሜን ፣ ደንማርኮች ፣ ወደ ፣ አይስላንድ ፣ ሄዱ ፤ ከአይስላንድ ፣ ወደ ፣ ግሪንላንድ ፣ ደረሱ ። ከዚያ ፣ ዛሬ ፣ ዩናይትድ ፣ እስቴትስ ፣ ወደተባለው ፣ አሜሪካ ፣ ገቡ ። ይህም ፣ የሆነው ፣ በሺ ፣ ዓመት ፣ ከልደት ፣ በኋላ ፣ ነው ። ይህም ፣ ልዩ ፣ ጉዞ ፣ እስከ ፣ ጥቂት ፣ ዓመታት ፣ ድረስ ፣ ለኤውሮጳውያን ፣ አልታወቀም ፣ ነበር ።

፪ ፡ ይህ ፣ እንደ ፣ ሥዕል ፣ ጐልቶ ፣ የሚታየው ፣ ሰውዬ ፣ በጣልያን ፣ አገር ፣ በሺ ፣ ፬፻፶፩ ፡ በጀኔባ ፣ ተወለደ ። በደገ ፣ ጊዜ ፣ በታላቅ ፣ ጥንቃቄ ፣ ጂዎግራፊ ፣ ተማረ ። መጀመርያ ፣ ልቡን ፣ የነካው ፣ ነገር ፣ በዚህ ፣ በሰፊው ፣ ውቅያኖስ ፣ ላይ ፣ ከሁን ፣ በፊት ፣ ያልተገኘ ፣ አንድ ፣ አገር ፣ ሳይኖር ፣ አይቀርም ፣ ብሎ ፣ አሰበ ።

፫ ፡ ኮሎምቡስ ፣ ደኃ ፣ ሰው ፣ ስለ ፣ ነበረ ፣ እነዚያን ፣ አገሮች ፣ ለማግኘት ፣ የሚበቃ ፣ ገንዘብ ፣ አልነበረውምና ፣ ለዚሁ ፣ ነገር ፣ እንዲረዱት ፣ ላገሩ ፣ ሹማምት ፣ ቢነግር ፣ አሳቡን ፣ የተቀበለው ፣ አላገኘም ። ከዚያም ፣ ወደ ፣ ፖርቱጋል ፣ ቢሄድ ፣ በዚያም ፣ የተሻለ ፣ ነገር ፣ አላገኘም ።

፬ ፡ በመጨረሻ ፣ ወደ ፣ እስጳንያ ፣ አደባባይ ፣ ሄደ ። የዚሁ ፣ አገር ፣ ንጉሥና ፣ ንግሥት ፣ ፌርዲናንድና ፣ ኤልዛቤል ፣ ናቸው ። ንጉሡ ፣ የኮሎምቡስን ፣ አሳብ ፣ እንደ ፣ ሌሎቹ ፣ ሰዎች ፣ ቸል ፣ ብሎት ፣ ቀልደና ፣ ለግጥ ፣ አደረገው ።

፭ ፡ ንግሥቲቱ ፣ ግን ፣ አሳቡን ፣ ተቀበለችውና ፣ የመንገዱን ፣ ኪሣራ ፣ ልትከፍል ለት ፣ ያላትን ፣ አልማዝና ፣ የከበረ ፣ ደንጊያ ፣ ሸጠች ። መርከቦቹ ፣ ፻ ፣ ሰዎችና ፣ የዓመት ፣ ሥንቃቸውን ፣ ብቻ ፣ የሚይዙ ፣ ነበሩ ። ኮሎምቡስ ፣ ዋና ፣ ሆኖ ፣ ነሐሴ ፣ ፫ኛ ፣ ቀን ፣ ሺ ፣ ፬፻፺፪ ፣ በመርከብ ፣ ለመጓዝ ፣ ከእስጳንያ ፣ ተነሣ ።

፮ ፡ መጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ አቃንቶ ፡ እየቀዘፈ ፡ ሄዶና ፡ ከናሪ ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ ደሴት ፡ ደረሰ ።

ከዚያ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ አቃና ። ጥቂት ፡ ሳምንት ፡ ከሆናቸው ፡ በኋላ ፡ የተወለዱበትን ፡ አገር ፡ ተመልሰው ፡ የሚያገኙት ፡ ስለ ፡ አልመሰላቸው ፡ ጓደኞቹ ፡ እንጐራጐሩበት ። እንዲያው ፡ በባሕር ፡ ተውጠው ፡ ይቀሩ ፡ ይመስላቸው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መሬትን ፡ ባይናቸው ፡ የሚያዩ ፡ አልመሰላቸውም ።

፯ ፡ ኮሎምቡስ ፡ ግን ፡ በ፫ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ አንዳች ፡ ምድር ፡ ወይም ፡ አገር ፡ ባናገኝ ፡ እንመለሳለን ፡ እያለ ፡ በጣም ፡ ያጽናናቸው ፡ ነበር ። በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ባሥር ፡ ሰዓት ፡ ከመርከቡ ፡ ላይ ፡ ቁሞ ፡ ሲመለከት ፤ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ ሲንተገተግ ፡ አየና ፡ ይህ ፡ እሳት ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ ሰይሆን ፡ አይቀርም ፡ አለ ። በበነጋው ፡ አንድ ፡ ደሴት ፡ ታየ ። ይህንንም ፡ ደሴት ፡ ኮሎምቡስ ፡ ስሙን ፡ ቅዱስ ፡ ሳልባዶር ፡ ብሎ ፡ ሠየመው ። ባላገሮቹ ፡ ግን ፡ ጓናሀና ፡ ይሉታል ።

፰ ፡ ይኸውም ፡ ከበሀማ ፡ ደቶሴች ፡ አንዱ ፡ ነው ። ባላገሮቹ ፡ ወደ ፡ ጠረፉ ፡ ተሰብስ በው ፡ ሦስቱን ፡ መርከቦች ፡ እያዩ ፡ ምንድር ፡ ይሆኑ ፡ እያሉ ፡ ይገረሙ ፡ ነበር ። ሕይወት ፡ ያላቸው ፡ ነገሮች ፡ እየመሰሉአቸው ፡ የመርከቦቹን ፡ ነጫጭ ፡ ሸራዎች ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ መላቸውን ፡ እነዚህ ፡ ክንፎቻቸው ፡ ናቸው ፡ አሉ ።

፱ ፡ ኮሎምቡስ ፡ ከመርከብ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ሲወርድ ፡ የከበረ ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ የተመ ዘዘ ፡ ሰይፍ ፡ በእጁ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ መሬቱን ፡ ሲረግጥ ፡ መጀመርያ ፡ ተንበርክኮ ፡ ጠረ ፉን ፡ ሳመ ። ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ክርስትና ፡ በአረማውያን ፡ ስፍራ ፡ የመግባቱ ፡ ምሳሌ ነው ፡ ሲል ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ መስቀል ፡ ተከለ ። ደሴቱም ፡ የንግሥት ፡ ኤዛቤ ላ ፡ ገንዘብ ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ አስታወቀ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሌሎችን ፡ ደሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ከጐበኘ ፡ በኋላ ፡ ባየውም ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አሳብ ፡ ለመስጠት ፡ ወደ ፡ እስጴን ፡ ተመለሰ ። ሁለተኛም ፡ ደግሞ ፡ ተመለሰ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የአሜሪካ ፡ የብስ ፡ መገኘት ፡ እስከ ፡ ፫ኛ ፡ ጕዞ ፡ አልቈየም ።

፲ ፡ ኮሎምቡስ ፡ በውነት ፡ ከባሕር ፡ ወዲያ ፡ አዲስ ፡ ዓለም ፡ መኖሩን ፡ ከሙግለጡ ፡ ወዲያው ፡ አያሎች ፡ መርከበኞች ፡ ወደዚያ ፡ ከመገሥገሥ ፡ አልቈዩም ። አሜሪ ኩስ ፡ ቬስፑሲውስ ፡ የተባለ ፡ የፍሎሬንስ ፡ ሰው ፡ አገሩ ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡ ስም ፡ እንዲ ጠራ ፡ እየዞረ ፡ ብልሀት ፡ ሠራ ።

፲፩ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያለ ፡ አገሩ ፡ ከሰሜን ፡ እስከ ፡ ደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ ታወቀ ። ከኤ ውሮጳ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራና ፡ ነገድ ፡ እየሄዱ ፡ መኖሪያቸውን ፡ በዚያ ፡ አደረጉ ። ሕዝብ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ የመግባታቸውን ፡ ታሪክ ፡ ከመተረኬ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወገን ፡ የነበሩትን ፡ የጥንት ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ ታሪክ ጨምሬ ፡ ለመተረክ ፡ እጀምራለሁ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ በመላ ፡ ያለማስረጃ ፡ ምን ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ፡ ?
ደንማርኮች ፡ አሜሪካንን ፡ የጐበኙት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ክሪስቶፈር ፡ ኮሎምቡስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፪ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተወለደ ፡ ? የተወለደበት ፡ ስፍራ ፡ የት ፡ ነው ፡ ?
በመርከቧ ፡ ገብቶ ፡ እስኪሄድ ፡ የነበረውን ፡ የኮሎምቡስን ፡ ታሪክ ፡ ተናገር ።

፫ ፡ መጀመሪያ ፡ በወዴት ፡ አድርጎ ፡ አቃንቶ ፡ ቀዘፈ ፡ ? ሰዎቹ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ኮሎምቡስ ፡ ያበራታቸው ፡ ነበር ፡ ?
መጀመርያ ፡ ያገኘው ፡ መሬት ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?

፬ ፡ ሕዝቡ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?

፭ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኮሎምቡስ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፲ ፡ አሜሪኩስ ፡ ቬስፑሲዩስ ፡ የተባሉ ፡ ምንድናቸው ፡ ?

፲፩ ፡ ሌሎችስ ፡ የተገኙት ፡ ምንድናቸው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፹፫ ፡ አሜሪካ ።

### ስለ ፡ አይስላንድና ፡ ስለ ፡ ግሪንላንድ ፡ ስለ ፡ ፈረንሳዎችም ፡ ባሜሪካ ፡ መግባት ።

፩ ፡ አንድ ፡ የኖርዌ ፡ የባሕር ፡ ወንበዴ ፡ በ፰፻፰ ፡ አይስላንድ ፡ የተባለውን ፡ ደሴት ፡ አገኘ ፡ ብዬ ፡ ፊት ፡ ነግሬያችኋለሁ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የኖርዌ ፡ ሰዎች ፡ ወደዚያ ፡ እየሄዱ ፡ ለመኖር ፡ ከመሄድ ፡ አላቋረጡም ። አገሩ ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ ብርዳም ፡ ነው ። በደሴቱ ፡ ላይ ፡ ሄክላ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እሳትና ፡ ጢስ ፡ አመድም ፡ የሚተፋ ፡ በመናወጡም ፡ ምክንያት ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡ ለማየት ፡ ደስ ፡ የማያሰኝ ፡ ተራራ ፡ አለ ።

፪ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ ሕዝቡ ፡ በዚያ ፡ ከመብዛት ፡ አላቋረጡም ። ክርስትናም ፡ በ፲፻፹፩ ፡ ዓመት ፡ በመኻከላቸው ፡ ተሰበከ ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምረው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ መልካም ፡ ሕዝብ ፡ ከመባል ፡ ሳያቋርጡ ፡ ይኖራሉ ። የሕዝብ ፡ ቍጥር ፡ ፰፰ ፡ ሺሕ ፡ ናቸው ። በደንማርክ ፡ መንግሥት ፡ ይገዛሉ ።

፫ ፡ ግሪንላንድም ፡ የተገኘው ፡ በዚያው ፡ አይስላንድ ፡ በተገኘበት ፡ ዘመን ፡ ነው ። ወዲያው ፡ ሕዝብ ፡ ገባበት ፡ ወደዚያ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የገባው ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። በምዕራብ ፡ ወገን ፡ የገቡትን ፡ ሕዝብ ፡ ባላገሮች ፡ ባጠፉዋቸው ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ሺ ፡ ፫፻፲፩ ፡ ድረስ ፡ የቀኘው ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ እየበረቱ ፡ ሄዱ ። በሺ ፡ ፩፻፱ ፡ ደንማርኮች ፡ በየዓመቱ ፡ መርከቦች ፡ ወደ ፡ ግሪንላንድ ፡ እየሰደዱ ፡ የተነሣውን ፡ ሁከት ፡ ጸጥ ፡ አደረጉት ። የቀኚዎቹ ፡ አገሮች ፡ መርከቦች ፡ ስለ ፡ አልኖሩአቸው ፡ መገናኘታቸው ፡ ቀረ ።

እንዲሁም ፡ በምሥራቅ ፡ ወገን ፡ በገቡት ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ በገቡት ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ተደረገው ፡ ባላገሮቹ ፡ ጠልተዋቸው ፡ የተነሡባቸው ፡ ይመስላል ። በደቡብ ፡ ግሪንላንድ ፡ ጠረፍ ፡ ደንማርኮች ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ለማድረግ ፡ እስከ ፡ ሺ፯፻፳፩ ፡ ድረስ ፡ አልዘገዩም ።

በመጨረሻው ፡ የሕዝብ ፡ ቈጠራ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ በግሪንላንድ ፡ ፱ ፡ ሺሕ ፡ ነዋሪዎች ፡ ተገኝተዋል ። ከነዚህም ፡ አያሎቹ ፡ ኤውሮጳውያን ፡ ናቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ክረምቱ ፡ ብርቱ ፡ ሆኖ ፡ ባሕሩን ፡ የሚዘጋው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ በዚያ ፡ ይኖሩ ፡ ስለ ፡ ነበሩት ፡ ምንም ፡ አይታወቅም ። ምናልባት ፡ ገና ፡ ፊት ፡ ሁሉም ፡ ጠፍተው ፡ ይሆናሉ ። ይህም ፡ ክሎኒ ፡ በሰሜን ፡ ግሪንላንድ ፡ ነበር ። በደቡብ ፡ ግሪንላንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ቅኝ ፡ ተደረገ ። ይህም ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ባላገሮቹ ፡ በቍጥር ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። የሚበዙት ፡ በዚያው ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩት ፡ ኤስኪሞች ፡ የተባሉት ፡ ናቸው ፤ የቀሩትም ፡ ከኖርዌ ፡ እየፈለሱ ፡ የመጡ ፡ ናቸው ።

፬ ፤ ከአሜሪካ ፤ ክፍል ፡ አሁን ፡ ለታላቁ ፡ ለብሪታንያ ፡ መንግሥት ፡ የሚገዙት ፡ እንደሚከተሉት ፡ ናቸው ። ኖቫእስኮቲያ ፤ ኙብረንስዊክ ፤ ኙፋውንድላንድ ፤ የላይና ፡ የታች ፡ ካናዳ ፤ ኙብሪቴን ፤ የሁድስን ፡ ቤ ፡ ግዛቶች ፡ ናቸው ።

፭ ፤ ግዛቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ባንድነት ፡ ቢሆኑ ፡ ስፋታቸው ፡ የዩናይትድ ፡ እስቴትስን ፡ ስፋት ፡ ያህል ፡ ይሆናሉ ። በሰሜን ፡ ከአርክቲክ ፡ ውቅያኖስና ፡ ከባፊንስቤ ፤ በምሥራቅ ፡ ከአትላንቲክ ፤ በደቡብ ፡ ከዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፤ በምዕራብ ፡ ከረሺያን ፡ አሜሪካንና ፡ ከፓስፊክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ይዋሰናሉ ።

፮ ፤ ከዛሬው ፡ ዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ መጨረሻ ፡ በሰሜን ፡ ወገን ፡ ጥንት ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ገብተው ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩት ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ ነበሩ ። ከ፭፻ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ወደዚያው ፡ ጠረፍ ፡ ዓሣ ፡ የሚያመላልስ ፡ መርከብ ፡ ይሰዱ ፡ ነበር ።

፯ ፤ በሺ ፡ ፭፻፴፬ ፤ ጂምስ ፡ ካርቲየር ፡ የተባለ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ሴንት ፡ ሎሬንስ ፡ ወደም ትባል ፡ ስፍራ ፡ በመርከብ ፡ ሁኖ ፡ መጣና ፡ ምሽግ ፡ ሠርቶ ፡ ከረመ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በካናዳና ፡ በኖቫ ፡ እስኮቲያ ፡ ሰው ፡ እየመጣ ፡ መግባት ፡ ጀመረ ። ፬ኛ ፡ ሄንሪ ፡ የተባለው ፡ የፈረንሳይ ፡ ንጉሥ ፡ በካናዳና ፡ በዙሪያው ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ዋና ፡ ጠቅላይ ፡ ገዢ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገዛ ፡ ማርኪዳላርሽ ፡ የተባለውን ፡ ሰው ፡ ሾመው ።

፰ ፤ የክዌቤክ ፡ ከተማ ፡ በሺ ፡ ፮፻—፰ ፡ ተመሠረተ ። ከባሕር ፡ ፭፻ ፡ ማይል ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ በሴንት ፡ ሎሬንስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ተሠራ ፤ የተመሠረተውም ፡ ከዐለት ፡ ደንጊያ ፡ ላይ ፡ ነው ።

፱ ፤ ባገሩ ፡ ላይ ፡ የገቡት ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲያን ፡ ከተባሉት ፡ ከጥንት ፡ ባላገሮች ፡ ጋር ፡ ተስማምተው ፡ በወዳጅነት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ባላገሮቹ ፡ እያደኑ ፡ የሚያመጡትን ፡ የአውሬ ፡ ቆዳ ፡ ጕፍላ ፡ እየሸጡላቸው ፡ ይገበያዩ ፡ ነበር ።

ይህንንም ፡ ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ እየሰደዱ ፡ ከፍ ፡ ላለ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጡ ፡ ነበር ። ከፈ ረንሳዮቹ ፡ ወገን ፡ አያሎች ፡ የሕንዶቹን ፡ ሴቶች ፡ አገቡ ።

፲ ፤ እንግሊዝ ፡ በደቡብ ፡ ካናዳ ፡ መግባት ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ አረማውያን ፡ በእ ንግሊዞች ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ እንዲያደርጉ ፡ ፈረንሳዎች ፡ ያነሳሡዋቸውና ፡ ይቆ ሰቁሱዋቸው ፡ ነበር ። ፈረንሳዎችና ፡ እንዲያኖች ፡ ተክዌቤክ ፡ ወይም ፡ ከሞንት ሬያል ፡ እየመጡ ፡ ያዲሲቱን ፡ እንግሊዝ ፡ መንደሮች ፡ ያቃጥሉ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ባላገሮችንም ፡ ገደሉዋቸው ። እኵሌቶቹንም ፡ እየማረኩ ፡ ወደ ፡ ካናዳ ፡ ወሰዱዋቸው ።

፲፩ ፤ በሺ ፡ ፮፻፳፱ ፡ ሰር ፡ ዳዊት ፡ ኬት ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ክዌቤክን ፡ ይዞ ነበር ። በኋላ ፡ ለፈረንሳዎች ፡ መለሰላቸው ። ያዲሲቱ ፡ እንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መልሰው ፡ ለመውሰድ ፡ እንዳሾተሉ ፡ ነበር ።

፲፪ ፤ በሺ ፡ ፯፻፲፩ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በመርከብ ፡ አድርጎ ፡ አድሚራል ። ሰር ፡ ሆቫንድን ፡ ዎከር ፡ በተባለ ፡ መሪነት ፡ አስከትቶ ፡ ወደሴንት ፡ ሎሬንስ ፡ ብርቱ ፡ ጦር ፡ ሰደደ ። በመርከብ ፡ ተሳፍረው ፡ የነበሩት ፡ ወታደሮች ፡ ፯ ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

፲፫ ፤ እነዚህ ፡ በደኅና ፡ ደርሰው ፡ ቢሆኑ ፡ ምናልባት ፡ አገሪቱን ፡ ክዌቤክን ፡ አሳ ምረው ፡ ሳይዙዋት ፡ አይቀሩም ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ወንዙ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ወፍራም ፡ ጉም ፡ መጣና ፡ መርከቡን ፡ ሸፈነው ። ወዲያው ፡ ብርቱ ፡ ነፋስ ፡ ነፈሰና ፡ ስምንት ፡ ወይም ፡ ዘጠኝ ፡ ያህሉን ፡ መርከቦች ፡ ወስዶ ፡ በጠረፍ ፡ ካለው ፡ ዐለት ፡ ድንጊያ ፡ ላይ ፡ ተመተማቸው ።

፲፬ ፤ በበነጋው ፡ ፈረንሳዮች ፡ የሺሕ ፡ ወታደሮች ፡ ሬሳ ፡ በድንጊያ ፡ ላይ ፡ ክምር ፡ በክምር ፡ እየሆነ ፡ ከጠረፉ ፡ ተቆልሎ ፡ አገኙት ። እነዚህ ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደሮች ፡ በዚህ ፡ ባልታሰበ ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ ስለጠፉ ፡ እንግሊዞች ፡ አዝነው ፡ ካና ዳን ፡ ለመያዝ ፡ የነበረ ፡ አሳባቸው ፡ ተሰናከለባቸው ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ አይስላንድ ፡ የተገኘው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
ሄክላ ፡ የሚባለው ፡ ተራራ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

፪ ፤ በዚሁ ፡ ደሴት ፡ ክርስትና ፡ የታወቀው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ሕዝቡ ፡ እንዴት ፡ ናቸው ፡ ?
ግሪንላንድ ፡ የተባለው ፡ ደግሞ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

፫ ፤ በዚሁ ፡ ደሴት ፡ የገቡት ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
በደቡብ ፡ የገቡት ፡ ሕዝብ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
ሕዝቡ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይሆናሉ ፡ ?

፬ ፤ ብሪቲሽ ፡ አሜሪካ ፡ የያዛቸው ፡ አገሮች ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ ?

፭ ፤ ስፋታቸው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ወሰናቸውስ ፡ ?
፮ ፤ የፈረንሳይ ፡ ይዞታ ፡ የቱ ፡ ነው ፡ ?
፯ ፤ በ፲፯፻፷፫ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? የካናዳ ፡ ገዥ ፡ ተብሎ ፡ የተሾመው ፡ ማነው ?
፰ ፤ ክዌቤክ ፡ የተመሠረተው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ስፍራውስ ፡ ወዴት ነው ፡ ?
፱ ፤ ፈረንሳይና ፡ ህንዶች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?
፲ ፤ እንግሊዞችን ፡ ፈረንሳዎች ፡ እንደምን ፡ አደረጉዋቸው ፡ ?
፲፩ ፤ ክዌቤክ ፡ የተያዘው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? የያዘውስ ፡ ማነው ፡ ?
፲፪—፲፫-፲፬ ፤ በ፲፯፻፶፮ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? የዘመቻውንና ፡ የጉዞውን ፡ ታሪክ ፡ ገል
ጸህ ፡ ተናገር ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፱ ፡ አሜሪካ ።

### የፈረንሳዮችን ፡ ቅኚ ፡ አገሮች ፡ እንግሊዞች ፡ አሸንፈው ፡ እንደያዙዋቸው ።

፩ ፤ በፈረንሳይና ፡ በቀድሞ ፡ እንግላንድ ፡ መካከል ፡ ጦርነት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁም ፡ በዲሱ ፡ እንግላንድና ፡ አሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ በፈረንሳይ ፡ ቅኚ ፡ ግዛት ፡ መካከል ፡ ጦነት ፡ ይደረግ ፡ ነበር ። ፈረንሳዎች ፡ ብርቱ ፡ ምሽግ ፡ ሲሠሩ ፡ እንግሊዞች ፡ ወይም ፡ አሜሪኮች ፡ ያንን ፡ ለመያዝ ፡ ታላቅ ፡ ጥረት ፡ ያደርጋሉ ።

፪ ፤ ፈረንሳዎች ፡ ኬፕብሬቶን ፡ በተባለው ፡ ደሴት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ በጥንቃቄ ፡ መሽገውት ፡ የነበረውን ፡ የሉዊስቡርግን ፡ ከተማ ፡ በሺ ፡ ፯፻፵፭ ፡ ያዲሲቱ ፡ እንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ለመውሰድ ፡ አሰበው ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ሰበሰቡና ፡ ዊልየም ፡ ፔፔርል ፡ ለተባለ ፡ ላንድ ፡ ለቦስቶን ፡ ነጋዴ ፡ አበጋዝ ፡ ሆኖ ፡ እንዲዘምት ፡ የጦር ፡ አለቅነት ፡ ሰጡት ።

፫ ፤ ጦሩም ፡ በመርከብ ፡ እየገባ ፡ ሄደና ፡ ወደ ፡ ብሬቶን ፡ ደሴት ፡ ሲደርስ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወረደ ። የጄኔራል ፡ ፔፔርል ፡ ሰዎች ፡ ጭራሽ ፡ ገበሬዎች ፡ ነበሩ ። እርሱም ፡ ራሱ ፡ የምሽግን ፡ አያያዝ ፡ ጉዳይ ፡ የማያውቅ ፡ ነበር ።

፬ ፤ ያዲሲቱ ፡ እንግላንድ ፡ ሰዎች ፡ ብልሀት ፡ እንኳ ፡ ባይኖራቸው ፡ ብዙ ፡ ኀይል ፡ ነበራቸውና ፡ መድፋቸውን ፡ ጠምደው ፡ ሁለት ፡ ሳምንት ፡ ያህል ፡ ከተማውን ፡ በመድፍ ፡ ቢመቱት ፡ የፈረንሳይ ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ ባንዲራውን ፡ አወረደ ። የሉዊስቡርግም ፡ መሸነፍ ፡ እጅግ ፡ የማይታይ ፡ ሆኖ ፡ ታሰበ ።

፭ ፤ ጦርነቱ ፡ ከተጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ሉዊስቡርግ ፡ ለፈረንሳዮች ፡ ተመልሶላቸው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በሺ ፡ ፯፻፶፰ ፡ ጄኔራል ፡ ዎልፍ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መልሶ ፡ ያዘውና ፡

ወዲያው ፡ ቀጥሎ ፡ ይኸው ፡ ጀኔራል ፡ ክቤቤክን ፡ ለመያዝ ፡ የጦር ፡ ጭፍራ ውን ፡ ይዞ ፡ ተነሣ ።

፮ ፤ ከተማው ፡ በብርቱ ፡ ተመሽጎ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ይደፈራል ፡ የማይባል ፡ ነበር ። ለወታደርና ፡ ለጦር ፡ ዕቃ ፡ ማስቀመጫ ፡ ተብሎ ፡ በዐለት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተና በጣም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተሠራ ፡ ግንብ ፡ በከተማው ፡ ዙሪያ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ግንብና ፡ በፈረንሳይ ፡ ምሽግ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ በቀር ፡ ተግንብ ፡ ውጭ ፡ የነበረው ፡ የፈረንሳይ ፡ ጦር ፡ እጅግ ፡ ብዙ ነበር ።

፯ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ጀኔራል ፡ ዎልፍ ፡ ክቤቤክን ፡ ለመያዝ ፡ ወይም ፡ ሕይወቱን ፡ በዚሁ ፡ በጦርነቱ ፡ እስኪያሳልፍ ፡ ለመዋጋት ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ውጊያውን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ ከፈተነ ፡ በኋላ ፡ ጦሩን ፡ ከጠረፍ ፡ እየ መራ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ተጠጋ ። አፋፉን ፡ ዘልቆ ፡ ከሜዳው ፡ ሲደርስ ፡ ከጠራ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ አለው ፡ ወደ ፡ ክቤቤክ ፡ ግንብ ፡ ደረሰ ።

፰ ፤ ይህም ፡ የጀግንነት ፡ ሥራ ፡ የተሠራው ፡ በሌሊት ፡ ነበር ። የፈረንሳይ ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ መከበቡን ፡ እንደ ፡ ሰማ ፡ እንግሊዞችን ፡ ሊገጥማቸው ፡ ተሰናዳና ፡ ጦርነ ቱም ፡ ያን ፡ ጊዜውን ፡ ተጀመረ ።

፱ ፤ ጀኔራል ፡ ዎልፍ ፡ ከወታደሮቹ ፡ ፊት ፡ ቀድሞ ፡ በጀግንነት ፡ ወደፊት ፡ ይመ ራቸው ፡ ነበር ። ምንም ፡ ከሁለት ፡ ላይ ፡ ቢቈስል ፡ ከጦሩ ፡ ፊት ፡ አላፈገፍግም ፡ ብሎ ፡ አሻፈረኝ ፡ በማለት ፡ ሲዋጋ ፡ በመጨረሻው ፡ የመድፍ ፡ አረር ፡ መታ ውና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዘረጋው ።

፲ ፤ ጥቂቶች ፡ ወታደሮች ፡ ሆኑና ፡ የጦር ፡ ደጀን ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ ተሸክመው ፡ ወሰዱት ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ሞት ፡ እጁን ፡ ቢጭንበት ፡ በዙሪያው ፡ ያለውን ፡ የጦር ፡ ውካታና ፡ መሩዋርዋጥ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ የትኛው ፡ ወገን ፡ ነው ፡ የሚ ሸሸው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ።

፲፩ ፤ አንድ ፡ ወታደር ፡ የሚሸሹት ፡ ፈረንሳዎች ፡ ናቸው ፡ የኛ ፡ ጦር ፡ ድል ፡ አድርጓል ፡ ቢለው ፡ ጀኔራል ፡ ዎልፍ ፡ የደስታ ፡ ምልክት ፡ ከፊቱ ፡ ፈገግ ፡ ፍል ቅቅ ፡ አለና ፡ እንግዲህ ፡ የደስታ ፡ ሞት ፡ እሞታለሁ ፡ ብሎ ፡ ወዲያው ፡ በመ ጨረሻው ፡ ትንፋሽ ፡ ሕይወቱ ፡ ተለየች ።

፲፪ ፤ ፈረንሳዮች ፡ ፈጽመው ፡ ድል ፡ ሆኑ ። መሪያቸው ፡ ማርኪስ ፡ ደ ፡ ሞንት ካም ፤ የተባለ ፡ ክፉኛ ፡ ቈሰለ ፤ ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ክቤቤክ ፡ ተከበበ ። የፈረንሳይ ፡ ግዛት ፡ የነበረው ፡ መላው ፡ አውራጃና ፡ ደግሞም ፡ ፈረንሳይ ፡ በሰ ሜን ፡ በኩል ፡ የያዘው ፡ ሁሉ ፡ በእንግሊዝ ፡ እጅ ፡ ወደቀ ።

፲፫ ፤ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በእንግሊዝ ፡ ሲገዛ ፡ ኖረ ። በእንግሊዞች ፡ እጅ ፡ ተይዞ ፡ የነበረ ፡ ሌላው ፡ የአሜሪካ ፡ ግዛት ፡ እየተለቀቀ ፡ ነጻነቱን ፡ ሲያገኝ ፡ የጥንት ፡ የፈረንሳይ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ የነበረው ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ሲገዛ ፡ ይኖራል ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ በፈረንሳይና ፣ በእንግላንድ ፣ መኻከል ፣ የነበረው ፣ ግጭት ፣ ጥቅሙ ፣ ምንድነው ።
፪ ፤ ሉዊስቡርግ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ? በ፲፯፻፶፱ ፣ ምን ፣ ተደረገ ፣ ? የሉዊስ ቡርግን ፣ መያዝ ፣ ተናገር ።
፫ ፤ ለፈረንሳይ ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ተመለሰለት ፣ ?
ጀኔራል ፣ ዎልፍ ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ያዘው ፣ ?
፬ ፤ ስለ ፣ ክዌቤክ ፣ መያዝ ፣ ተናገር ።
፭ ፤ የፈረንሳይ ፣ ጦር ፣ መሪ ፣ ማነው ፣ ? የጀኔራል ፣ ዎልፍን ፣ አማሙዋት ፣ ተናገር ።
፮ ፤ የድሉ ፣ ፍጻሜ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?
የፈረንሳይ ፣ ይዞታ ፣ የነበረው ለማን ፣ ሆነ ፣ ?
፯ ፤ የቀድሞ ፣ የፈረንሳይ ፣ ቅኝ ፣ የነበረው ፣ ለማን ፣ ሆነ ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፲፫ ፣ አሜሪካ ።

### ስለ ፣ ዩናይትድ ፣ እስቴትስ ፣ ሁኔታ ።

፩ ፤ አሁን ፣ ስለ ፣ አሜሪካ ፣ እንናገራለን ። እስኪ ፣ አስቀድመን ፣ የምድርን ካርታ እንመልከት ። የአገርን ፣ ታሪክ ፣ ለማወቅ ፣ ስፍራውን ፤ ዳርቻውን ፤ መልኩን ፤ ወንዙንና ፣ ተራራውን ፣ ሁሉ ፣ መማር ፣ ይገባል ።

፪ ፤ ዩናይትድ ፣ እስቴትስ ፣ (የተባበሩ ፣ መንግሥታት ፣) ሲባሉ ፣ ከጥንት ፣ ቍጥራቸው ፣ ፵፰ ፣ ይሆናሉ ። በሰሜን ፣ ተእንግሊዝ ፣ ይዞታ ፤ በምሥራቅ ፣ ከአትላንቲክ ፣ ውቅያኖስ ፤ በደቡብ ፣ ተሜክሲኮ ፣ መንግሥታት ፤ በምዕራብ ፣ ተፓሲፊክ ውቅያኖስ ፣ ይዋሰናሉ ። አገሩ ፣ በስፋት ፣ መላውን ፣ ኤወሮፓን ፣ ያህላል ፻፴፰ ፣ ሚሊዮን ፣ የሚሆኑ ፣ ባላገሮች ፣ አሉበት ።

፫ ፤ የዛሬው ፣ ዩናይትድ ፣ እስቴትስ ፣ በአንድነት ፣ ሆነው ፣ የተባበሩ ፣ ፵፰ ፣ መንግሥታት ፣ ናቸው ። ሁሉም ፣ እያንዳንዱ ፣ ሕግና ፣ አገረ ፣ ገዢ ፣ አለው ። ደግሞ ፣ ዐሥር ፣ አገሮች ፣ አሉ ። ስማቸውም ፣ አላስካ ፤ አሪዞና ፤ ዳኮታ ፤ የኮሎምቢያ ፣ አውራጃ ፣ ኤዳሆ ፤ ሞንታና ፣ አዲስ ፣ ሜክሲኮ ፤ ኡታ ፤ ዋሽንግቶን ፤ ዮሚንግ ይባላሉ ። እነዚህ ፣ ሕዝቡ ፣ እጅግ ፣ ብዙ ፣ የሆኑ ፣ እንደሆን ፣ መንግሥታት ፣ ለመሆን ፣ ይመረጣሉ ። ሁሉም ፣ የሕዝብ ፣ መንግሥት ፣ ተብለው ፣ በነዚህ ፣ ላይ ፣ ዋና ፣ ገዢ ፣ የሚሆን ፣ አንድ ፣ ፕሬዚዳንት ፣ ይሾማል ።

፬ ፤ የዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ አገሮች ፡ ስማቸው ፡ በፊደል ፡ ሥርዓት ፡ ሲጻፉ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

አላባማ ፡
አርካንሳስ ፡
ካሊፎርኒያ ፡
ኮሎራዶ ፡
ኮኔክቲከት ፡
ሎዋ ፡
ካንሳስ ፡
ኬንቱኪ ፡
ሉዊሲያና ፡
ሜን ፡
ሜሪላንድ ፡
ማሳቹሲትስ ፡
ሚቺጋን ፡
ሚኔሶታ ፡
ሚሲሲፒ ፡
ሚሱሪ ፡
ኔብራስካ ፡
ኔቫዳ ፡
ኙሀምፕሸር ፡

ዴላዌር ፡
ፍሎሪዳ ፡
ጂዎርጂያ ፡
ኢሊኖይስ ፡
ኢንዲያና ፡
ኙጂርሲ ፡
ኙዮርክ ፡
ኖርት ፡ ካሎሪና ፡
ኦሀዮ ፡
ኦሬጎን ፡
ፒንሲልቫኒያ ፡
ሮድ ፡ አይላንድ ፡
ሳውት ፡ ካሮሊና ፡
ቴኔሲ ፡
ቴክሳስ ፡
ቬርሞንት ፡
ቬርጂኒያ ፡
ዌስት ቪርጂኒያ ፡
ዊስኮንሲን ፡

፭ ፤ ዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ምንም ፡ መኻከለኛውን ፡ አገር ፡ ቢይዝ ፡ ከዚሁ ከተወሰነው ፡ ሲሰው ፡ ባሕርና ፡ ውቅያኖስ ፡ ወደቦችም ፡ አሉበት ። ከነዚህም ዋኖቹ ፡ በጣም ፡ የታወቁት ፡ ቺሳፒክ ፡ ዴላዌር ፡ ማሳኩሲት ፡ ይባላሉ ። በሰሜን ወገን ፡ አየሩ ፡ መልካም ፡ ነው ። መሬቱም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጡ ፡ አታክልቶች ፡ ያበቅላል ። በደቡብ ፡ ወገን ፡ አገሩ ፡ሙቀት ፡ ነው ። ፓርቱካን ፤ በለስ ፤ ሎሚ ፡ ይገኝበታል ።

<u>ጥ ያ ቄ ።</u>

፩ ፤ ያገርን ፡ ታሪክ ፡ ለማወቅና ፡ ለመማር ፡ የሚያስፈልገው ፡ ምንድነው ፡ ?
፪ ፤ የዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ያገር ፡ ወሰን ፡ ከየት ፡ መለስ ፡ ነው ፡ ? ስፋቱስ ፡ ? የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ?
፫ ፤ ስንት ፡ መንግሥታት ፡ ይገኙበታል ፡ ?
ስንት ፡ ግዛቶች ፡ አሉ ፡ ?
አገዛዙ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፬ ፤ የመንግሥታቱ ፡ ስም ፡ ማንና ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ?
ገዛቶቹ ፡ እነዜት ፡ ናቸው ፡ ?
ዋናዎች ፡ የባሕር ፡ ከንዶች ፡ ስማቸው ፡ ማነው ፡ ?
አየሩና ፡ መሬቱ ፡ እንዴት ያለ ፡ ነው ፡ ?
ፍሬ ፡ ይሰጣልን ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፱ ፡ አሜሪካ ።

### ስለ ፡ አዲሲቱ ፡ እንግላንድ ፡ መግባትና ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ስለመያዝ ።

፩ ፤ ስለ ፡ መላው ፡ ዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ከመናገሬ ፡ በፊት ፡ የብዙ ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ አገባብ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አጭር ፡ አሳብ እሰጣችኋለሁ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ፊት ፡ የገቡ ፡ ባይሆኑ ፡ ከሰሜን ፡ ጫፍ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ከዲሲቱ ፡ እንግላንድ ፡ እጀምራለሁ ።

፪ ፤ አዲሲቱ ፡ እንግላንድ ፡ በምትባለው ፡ የሚገኙ ፡ አገሮች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ኙሀም ፤ ፕሼር ፤ ቬርሞንት ፤ ማሳቹሴትስ ፡ ሮድ ፡ አይላንድ ፡ ኮኔክቲከት ፡ ናቸው ።
በሰሜን ፡ ከታችኛው ፡ ካናዳ ፤ በምሥራቅ ፡ ከኙ ፡ ብሩንስዊክና ፡ ከአትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ በደቡብ ፡ ከአትላንቲክና ፡ ከሎንግ ፡ አይላንድ ፡ ሳውንድ ፤ በምዕራብ ፡ ከኙዮርክ ፡ ይዋሰናል ።

፫ ፤ በ፲፮፻፳ ፡ ሚፍላዎር ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ መርከብ ፡ ከያሉት ፡ ሹማምትና ፡ ደኅች ፡ ሰዎች ፡ ከሴቶችና ፡ ከሕፃናት ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ አዲሲቱ ፡ እንግላንድ ፡ ጠረፍ ፡ ደረሰ ። እነዚህም ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የወጡት ፡ በስደት ፡ ኑርአል ። እነዚህም ፡ እንደ ፡ አሳባቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ሌለበት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መሄዳቸው ፡ ነበር ።

፬ ፤ ይህ ፡ ሚፍላዎር ፡ የተባለ ፡ መርከብ ፡ ፕሊማውት ፡ ወደ ፡ ተባለ ፡ ወደብ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወራቱ ፡ ታኅሣሥ ፡ ጊዜውም ፡ ክረምት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ጽኑ ፡ ብርድ ፡ ነበር ። ሰዎቹም ፡ ወደ ፡ ጠረፉ ፡ ወጥተው ፡ ያረፉበት ፡ስፍራ ፡ መልካም ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ አይታረብም ።

፭ ፤ በዚያው ፡ ቦታ ፡ ሥራ ፡ ጀምረው ፡ ራሳቸው ፡ እየሠሩ ፡ ትንንሾች ፡ ጐጆዎች ፡ አቆሙ ። መጀመርያ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ አገኛቸው ። ብዙዎቹ ፡ እየታመሙ ፡ ሙተዋል ። የዳኑትም ፡ ምግብ ፡ አጥተው ፡ ይራቡ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ከባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ያሣ ፡ ቅርፊት ፡ እየቀረፉ ፡ ለመመገብ ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው ።

፮ ፤ በዚሁ ፡ ችግራቸው ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኢንዲያኖች ፡ ሊወጉአቸው ፡ ያስፈራሩዋቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ መናንያን ፡ በጽድቃቸው ፡ መጠን ፡ እንዲሁ ፡ ትዕግሥታቸውና ፡ ጀግንነታቸው ፡ የበዛ ፡ ነበር ። እምነታቸውን ፡ በእግ ፡ ዚአብሔር ፡ አድርገው ፡ ባገሩ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንኖርበታለን ፡ ብለው ፡ በማሰብ ፡ በጸጥታ ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ።

፯ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ቀጥለው ፡ ሌሎች ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ የሃይማኖት ፡ ሰዎች ፡ በዲሲቱ ፡ እንግላንድ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ መግባት ፡ ጀመሩ ፡ እኩ ሌቶቹ ፡ በሳሌም ፤ ሌሎችም ፡ በቦስቶን ፡ ገቡ ።

፰ ፤ በ፲፻፮፻፴፮ ፡ ስድሳ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ከነልጆቻቸው ፡ በዚያ ፡ ገብተው ፡ ለመኖር ፡ ከማሳቹሴት ፡ ተነሥተው ፡ ከብቶቻቸውን ፡ አስቀድመው ፡ በፊታቸው ፡ እየነዱ ፡ በእግራቸው ፡ በደን ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ኮኔክቲከት ፡ ተጓዙ ። ሌሊትም ፡ በዛፍ ፡ ሥር ፡ ያድሩ ፡ ነበር፡ እንጂ ፡ የሚጠጉበት ፡ ማደሪያ ፡ አላገኙም ። ወደ ኮኔክቲከት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ዌንድሶርንና ፡ ሀርትፎርድን ፡ ሌሎችንም ፡ ከተሞች ፡ መሥራት ፡ ጀመሩ ። መጀመሪያ ፡ በኮኔክቲከት ፡ ገብተው ፡ የተቀመጡ ፡ እነዚህ ናቸው ።

፱ ፤ በ፲፻፮፻፴፮፡ አንድ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ እርሱም ፡ ካህን ፡ የሆነ ፡ ባብቲስት ፡ ከሚ ባሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ወገን ፡ የበለቀኔው ፡ ሚልትን ፡ ወዳጅ ፡ የነበረ ፡ ሮጀር ፡ ዊልየም ፡ የተባለ ፡ ከማሳቹሲት ፡ ተሰዶ ፡ ወደ ፡ ሮድ ፡ አይላድ ፡ ሄዶና ፡ የሃይ ማኖትን ፡ ነጻነት ፡ ወደሚያቆምበት ፡ ወደ ፡ ፕሮቪደንስ ፡ ተቀመጠ ። ይህ ፡ መል ካም ፡ ሰው ፡ ለኢንዲያኖች ፡ ታላቅ ፡ ወዳጅ ፡ ሆነ ፤ እነርሱም ፡ ከርሱ ፡ ጋር፡ጽኑ ወዳጅነት ፡ አደረጉ ።

፲ ፤ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያሉ ፡ ባዲሲቱ ፡ እንግላንድ ፡ ጠረፍ ፡ ለጠረፍ ፡ አያሎች ፡ መን ደሮች ፡ ተሠሩ ። በዶሴቱ ፡ የተገኙት ፡ ወንዞች ፡ ሁሉ ፡ የሰዎች ፡ መኖሪያ ፡ መሆ ናቸው ፡ ተመረመረ ። ከአገሩ ፡ የሚበልጠውን ፡ ክፍል ፡ ደን ፡ አልብሶት ፡ ነበር ። በቤቶቹ ፡ ዙሪያ ፡ ቀበሮችና ፡ ሌሎችም ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ ሲጮሁ ፡ ያድሩ ፡ ነበር ።

## ጥያቄ ።

፱ ፤ አዲሲቱ ፡ እንግላንድ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ?
ዳርቻው ፡ የት ፡ ይደርሳል ፡ ?

፲ ፤ በ፲፮፻፳ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?
በፔሊማውት ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ገባበት ፡ ተናገር ።

፯ ፤ ሌሎቹ ፡ ሕዝብ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
በ፲፮፻፴፮ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ?

፱ ፤ ፕሮቪዲን ፡ በሚባለው ፡ አውራጃ ፡ ማን ፡ ገባበት ፡ ?

፲ ፤ እያደር ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ምንድነው ፡ ?
አዲሲቱ ፡ እንግላንድ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፱፻፺ ፡ አሜሪካ ።

### ያዲሲቱ ፡ እንግላንድ ፡ ታሪክ ፡ ይቀጥላል ።

፩ ፤ ባዲሲቱ ፡ እንግላንድ ፡ የገቡት ፡ ሕዝብ ፡ ደጎች ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከነዚሁ ፡ ብዙዎቹ ፡ ኢንዲያኖቹን ፡ ከዱር ፡ አራዊት ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ የላቸውም ፡ ይሉዋቸው ፡ ነበር ።

፪ ፤ ለህንዶች ፡ ጆን ፡ ኢሊዎት ፡ ከሚባለው ፡ ሰውየ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ወዳጅ ፡ አልነበራቸውም ። እርሱ ፡ እንደጓደኞቹ ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ አሰባቸው ፡ እየዞረ ፡ ይሰብክላቸው ፡ ነበር ። መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በቋንቋቸው ፡ ሲተረጒምና ፡ አነባበቡንም ፡ ለኢንዲያኖች ፡ ሲያስተምራቸው ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ኖረ ፡ የኢንዲያኖች ፡ ሐዋርያ ፡ ተባለ ።

፫ ፤ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከነጮች ፡ ወገን ፡ ህንዶቹን ፡ የሚወዱ ፡ ጥቂቶች ፡ ነበሩ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ህንዶቹ ፡ እንደ ፡ ጠላት ፡ ቈጥረዋቸው ፡ ደናችንን ፡ ሁሉ ፡ እየመነጠሩ ፡ እርሻ ፡ ያደርጉትና ፡ አውሬ ፡ የምናድንበት ፡ ያሳጡናል ፡ ብለው ፡ ይፈሩ ፡ ነበር ።

፬ ፤ ስለዚህ ፡ ገቢዎቹ ፡ ከህንዶች ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይዋጉ ፡ ነበር ። ከመቸውም ፡ ይልቅ ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ ያደረጉት ፡ በሺ ፡ ፯፻፸፭ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የንጉሥ ፡ ፊልጵ ፡ ጦርነት ፡ ይባላል ። ንጉሥ ፡ ፊልጵ ፡ ምንም ፡ ህንዳዊ ፡ ቢሆን ፡ ታላቅ ፡ ማስተዋል ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነበርና ፡ ባገሩ ፡ ው ስጥ ፡ የገቡትን ፡ ነጮች ፡ አጥፍቶ ፡ አዲሲቱን ፡ እንግላንድ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ለማድረግ ፡ አስቦ ፡ ነበር ።

፭ ፤ ንጉሥ ፡ ፊልጵ ፡ መጀመሪያ ፡ ሕዝቡ ፡ በጾም ፡ ቀን ፡ ከሚሰበሰቡበት ፡ ሲወጡ ፡ በማሳኩሴትስና ፡ በስዋንዚ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ወደቀባቸውና ፡ ስምንት ፡ ወይም ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዎች ፡ በ ጦርስ ፡ ወደቁ ፤ ብዙዎቹ ፡ ተገደሉ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ጠፉ ፤ አያሌ ፡ ቤቶችም ፡ ተቃጠሉ ።

፮ ፤ ባዲሲቱ ፡ እንግላንድ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ብረት ፡ አንሥቶ ፡ ንጉሥ ፡ ፊልጵን ፡ ለመውጋት ፡ ወጣ ። ጆን ፡ ኤሌድት ፡ እንዳደረገው ፡ ህንዶቹን ፡ ማስተማርና ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍን ፡ ማስነበብ ፡ ትተው ፡ መምህራን ፡ እንኳ ፡ ሳይቀሩ ፡ በተቻላቸው ፡ ዐቅም ፡ ለመዋጋት ፡ ጠመንጃቸውን ፡ እያነገቱ ፡ ወጡ ።

፯ ፤ ወዲያው ፡ በሚመጣው ፡ ክረምት ፡ ነጮቹ ፡ ፪ሺ ፡ ጦር ፡ አሰናዱና ፡ ንጉሥ ፡ ፊልጵንና ፡ ሌሎችን ፡ ህንዳውያን ፡ ሁሉ ፡ ሮድ ፡ አይላንድ ፡ ወደሚባለው ፡ ብርቱ ፡ ምሽግ ፡ ነዱዋቸው ። ይህም ፡ በረግረግ ፡ መካከል ፡ ሆኖ ፡ ፭፻—ቤቶች ፡ የአሉበት ፡ ነው ። በዚያም ፡ የህንዶቹ ፡ ሴቶችና ፡ ልጆች ፡ ተጠግተው ፡ ነበሩ ።

፰ ፤ በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ፬ሺ ፡ ጀግኖች ፡ ከህንዶች ፡ ነበሩ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ስደተኞቹ ፡ ነጮቹ ፡ በጀግንነት ፡ ተዋግተው ፡ ምሽጉን ፡ ሰብረው ፡ ቤቱንና ህንዳውያን ፡ የሆኑትን ፡ ብዙዎችን ፡ ድውያን ፡ ሴቶችንና ፡ ሕፃናትን ፡ ከነሕይወታቸው ፡ አቃጠሉዋቸው ።

፱ ፤ የሞቱትና ፡ የቈሰሉት ፡ ህንዶች ፡ ፩ሺ ፡ ይሆናሉ ። አያል ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ ተማረኩ ። የቀረቱም ፡ ሸሽተው ፡ አመለጡ ። የምሽጉን ፡ ውስጥ ፡ ለማየት ፡ እጅግ ፡ ያስፈራ ፡ ነበር ። ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ሕፃናትም ፡ ግማሽ ፡ አካላታቸው ፡ ተቃጥሎ ፡ ባመድ ፡ ውስጥ ፡ ተጠብሶ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

፲ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሡ ፡ ፊልጽ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ በሕይወት ፡ ነውና ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ጦርነቱ ፡ አላለቀም ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ በሚመጣው ፡ በጋ ፡ ርድ ፡ በተባለ ፡ ደሴት ፡ በሆድ ፡ ተራራ ፡ መጠጋቱ ፡ ታውቆ ፡ ነበርና ፡ ካፒቴን ፡ ቸርች ፡ የተባለ ፡ ጥቂት ፡ ሰው ፡ ይዞ ፡ ሲያሳድደው ፡ ካሜሪኮች ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ህንዳዊ ፡ ተኵሶ ፡ መታው ።

፲፩ ፡ ከዚህ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ህንዶች ፡ የአዲስ ፡ እንግላንድን ፡ ሕዝብ ፡ ለማስቸገር ፡ አልቻሉም ። ቢሆንም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሌሊት ፡ በደን ፡ ውስጥ ፡ ሹልከ ፡ እያሉ ፡ እየመጡ ፡ ቤት ፡ ማቃጠላቸውንና ፡ ሰው ፡ መግደላቸውን ፡ አልተዉም ። ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ያዲሱ ፡ እንግላንድ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ በፍጥነት ፡ እየበዛ ፡ ሄደና ፡ በገሩ ፡ ለጊዜው ፡ ያማሩ ፡ መንደሮችና ፡ ከተሞች ፡ ተሠሩበት ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ተውጭ ፡ የመጡት ፡ ሕዝብ ፡ ህንዶችን ፡ ምን ፡ ያስቡዋቸዋል ፡ ?
፪ ፤ ጆን ፡ ኤሊዎት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፫ ፡ ህንዶች ፡ ነጮችን ፡ ምን ፡ አሰቡዋቸው ፡ ?
፬ ፡ የንጉሥ ፡ ፊልጽ ፡ ጦርነት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተጀመረ ፡ ?
ንጉሥ ፡ ፊልጽ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፭ ፤ መጀመርያ ፡ አሜሪኮችን ፡ የወረራቸው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
፮ ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
ቈይተው ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
፯ ፤ እንዴት ፡ ያለ ፡ ምሽግ ፡ ነበራቸው ፡ ?
፰—፱ ፤ ምሽጉ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ ተናገር ።
፲ ፤ የንጉሥ ፡ ፊልጽን ፡ ፍጻሜ ፡ ተናገር ።
፲፩ ፤ ከዚህ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ህንዶች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

## ምዕራፍ ፤ ፲፫ ፡ አሜሪካ ።

### የቀድሞ ፡ ቤርጂኒያ ፡ ታሪክ ።

፩ ፤ ከአዲሱ ፡ እንግላንድ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከጥቂት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የቤርጂኒያ ፡ ቅኝ ፡ በተያዘ ፡ ጊዜ ፡ በሺ ፡ ፲፭፻፹፱ ፡ ሰር ፡ ዎልትር ፡ ራሌፍ ፡ የተባለ ፡ በዚያ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ አኑሮ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በሽታ ፡ ጨረሳቸው ። በሺ ፡ ፲፭፻፺፱ ጀምስታውን ፡ የተባለውን ፡ ከተማ ፡ በጀምስ ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ ካፒቴን ፡ ክሪስቶፈር ፡ ኔውፖርት ፡

መሠረተው ። ህንዶቹ ፡ የገቡትን ፡ የውጭ ፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ አስቸገሩዋቸው ። ካፒቴን ፡ ጆን ፡ እስሚት ፡ ባይኖር ፡ ጭራሽ ፡ ያጠፉዋቸው ፡ ነበር ።

፪ ፡ ካፒቴን ፡ እስሚት ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ነበር ። እርሱም ፡ ወደ ፡ ቬርጂኒያ ፡ ሳይመጣ ፡ ቱርኮችን ፡ በጀግንነት ፡ የወጋ ፡ ነው ። ከህንዶቹ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ሁኖ ፡ ሲዋጋ ፡ ጀግንነቱን ፡ በትክክል ፡ አሳይቶአል ።

፫ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ካፒቴን ፡ እስሚት ፡ ከአያሎች ፡ አረማውያን ፡ ዘንድ ፡ ተለይቶ ፡ ሲመለስ ፡ ካንድ ፡ ረግረግ ፡ ስፍራ ፡ ደረሰና ፡ ተማጥ ፡ ውስጥ ፡ ተሥረግርጎ ፡ አንገቱ ፡ ድረስ ፡ ገብቶ ፡ ተወደወደ ። ህንዶች ፡ ከዚያ ፡ አወጡትና ፡ ፓህታን ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ ንጉሣቸው ፡ የሰንሰ ፡ ተሸከመው ፡ ወሰዱት ።

፬ ፡ ፓህታንም ፡ ከእንግሊዝ ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ የሚፈራው ፡ እርሱን ፡ ነበርና ፡ እንኳን ፡ እጄ ፡ ላይ ፡ ገባልኝ ፡ በማለት ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ። ያን ፡ ጊዜውን ፡ ሊገድለው ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረገና ፡ ወዲያው ፡ የካፒቴን ፡ እስሚት ፡ ሁለቱ ፡ እጆቹ ፡ ታሰሩ ። ራሱንም ፡ ከታላቅ ፡ ደንጊያ ፡ ላይ ፡ አደረጉና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዘረጉት ።

፭ ፡ ንጉሥ ፡ ፓህታን ፡ መቸም ፡ በኀይሉና ፡ በሰውነቱ ፡ ታላቅነት ፡ የሚመስለው ፡ የለም ። ካፒቴን ፡ እስሚትን ፡ ለመግደል ፡ ዱላ ፡ ይዞ ፡ ተነሣና ፡ ለመምታት ፡ ሲቃጣ ፡ ፒካሆንታስ ፡ የተባለች ፡ ሴት ፡ ልጁ ፡ ወደርሱ ፡ ፈጥና ፡ ገሠገሠች ።

፮ ፡ ይህች ፡ እጅግ ፡ ውብ ፡ የነበረች ፡ ህንዳዊት ፡ ቆንጆ ፡ ሂዳ ፡ በካፒቴን ፡ እስሚት ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ወደቀችና ፡ ምሕረት ፡ እንዲደረግላት ፡ አባትዋን ፡ በለመነችው ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ጉዴተኛ ፡ ህንድ ፡ እንባዋንና ፡ ልመናዋን ፡ አልተቃወመም ።

፯ ፡ ስለዚህ ፡ ካፒቴን ፡ እስሚት ፡ ተፈትቶ ፡ ወደ ፡ ጀምስታውን ፡ እንዲመለስ ፡ ተፈቀደለት ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የፒካሆንታስ ፡ ስም ፡ ሁለጊዜ ፡ በቬርጂኒያ ፡ እንደ ፡ ተከበረ ፡ ኖረ ። በኋላም ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ተገቡት ፡ እንግሊዞች ፡ አንድ ፡ እንግሊዛዊ ፡ አገባት ። የርስዋ ፡ ዘሮች ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በቬርጂኒያ ፡ እንደ ፡ ተከበሩ ፡ ይኖራሉ ።

፰ ፡ እስከ ፡ ቀድሞ ፡ ፈረንሳይ ፡ ጦርነት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የቀረውን ፡ የቬርጂኒያን ፡ ታሪክ ፡ አልፌዋለሁ ። ይህም ፡ በሺ ፡ ፯፻፶፭ ፡ ተጀመረ ፤ በቬርጂኒያ ፡ እንደሚታወቅ ፡ በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ዋናው ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ብራዶክ ፡ የተባለ ፡ የእንግሊዝ ፡ ጀኔራል ፡ ድል ፡ መሆኑና ፡ ፈረንሳዎችና ፡ አሚሪኮች ፡ ባሸመቁበት ፡ ስፍራ ፡ ወድቆ ፡ ከሰዎቹ ፡ አያሎቹ ፡ መገደላቸው ፡ ነው ። ኮሎኔል ፡ ዋሽንግቶን ፡ የተባለ ፡ በኋላ ፡ የተከበረ ፡ ጀኔራል ፡ የሆነ ፡ የሸሹትን ፡ ወታደሮች ፡ በመመለስ ፡ ታላቅ ፡ የከበረ ፡ ስም ፡ አገኘ ።

<u>ጥያቄ ።</u>

፩ ፡ በጀምስ ፡ ታውን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ገባበት ፡ ?
፪ ፡ ህንዶች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?